# እውነት

እውነት ቅጽ 1 ቁጥር 1

1993 ዓ.ም.

## በወቅታዊ ዓምዶች


| | |
|---|---|
| እውነት አርነት ያወጣችኋል  | 1 |
| አምላካዊ መልስ | 1 |


## በቋሚ ዓምዶች


| | |
|---|---|
| አገልግሎት  የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነው | 3 |
| ቤተክርስቲያን  ቤተክርስቲያን በማቴ 16 | 5 |
| አምልኮት  ለጌታ ለአምላክህ ስገድ | 7 |
| በረከት - ጥበብ  - ስለ እርሷ - ቅኔ ለበጉ - ሐኪሙን ወይስ.. - ስለ ክርስቶስ ... | 14 |


# እውነት አርነት ያወጣችኋል

«ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ እናንተ በቤ ብትኖሩ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል» አላቸው/ዮሐ.8፡31/።

የተለያየ የባርነት ቀንበር ተጭኖአቸው እየተጨነቁ የሚገኙና በአእምሮአቸው ሰላም አጥተው የሚኖሩ ሰዎች የሚመኙት ዋነኛ ነገር ቢኖር ቀንበሩን ሰብሮ ከተያዙበት ባርነት አርነት የሚያወጣቸውን ነገር ነው። «ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነው» ተብሎ እንደተጻፈው/2ጴጥ.2፡19/ ብዙ ወገኖች ከሥጋ ድካም የተነሣ ተሸንፈው ለማይፈልጉትና ለሚጐዳቸው ዓለማዊ ነገር በባርነት ሲገዙ ይታያል። በተራኒው ደግሞ የተያዙበትን የጥፋት ባርነት የማያስተውሉ ከሚኖሩበት የባርነት ኑሮ ጋር ተስማምተው በሃይማኖተኛነት ስሜት ብቻ ትምክህተኞች ሆነው የሚኖሩ ወገኖችም ይኖራሉ፤ እነዚህ ደግሞ «እውነት አርነት ያወጣችኋል» ብሎ ጌታ ባስተማራቸው ጊዜ «የአብርሃም ዘር ነን ለአንድም ስንኳ ከቶ ባሪያዎች አልሆንም፤ አንተ አርነት ትወጣላችሁ እንዴት ትላለህ?» ብለው የመለሱለትን አይሁድ ይመስላሉ /ዮሐ.8፡33/። ለእነርሱ እጅግ ጠሚ የሆነውን የአርነት ዜና ሲሰሙ «የአብርሃም ዘር ነን» በሚለው የወገኛነት ስሜት ተይዘው ይህን ተራኒ መልስ መስጠታቸው አሳዛኛ ነው። ከዚህ ይልቅ የኃጢአት ባሪያ መሆናቸውን አምነው አርነትን ቢፈልጉ ኖሮ ከተያዙበት ባርነት አርነት የሚያወጣቸውን እውነት ሊያውቁ በቻሉ ነበር። ብዙዎች አርነት ወደሚያወጣው እውነት ዘወር እንዳይሉ ዋነኛ ምክንያቱ ያሉበትን የባርነት ኑሮ አለማስተዋልና፣ በባርነት እንዳሉ ማመንን እንደውርደት መቊጠራቸው ነው።

ጌታችን በመቀጠል ከተናገራቸው ቃት እንደምንረዳው «እውነት አርነት ያወጣችኋል» እያለ የሚናገራቸው አይሁድ በኃጢአት ባርነት ውስጥ የነበሩሰዎች ናቸው። ኢየሱስን ሊገድሉት መፈለጋቸው የኃጢአት ባሪያዎች እንደሆኑ በትክክል ያስረዳልና /ቁ.34-38/። እነዚህ አይሁድ በጌታ ትምህርት ያመኑ እንደነበሩ ተገልጧል /ቁ.30-31/። ይሁንና ከነበሩበት የኃጢአት ባርነት ገና አርነት አልወጡም ነበር። ዛሬም እንዲሁ ነው፤ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የሚሰሙና የሚያምኑ ነገር ግን ገና በብዙ የጥፋት ባርነት ሥር የሚኖሩ ብዙዎች ናቸው። ከእነዚህም አንዳንዶቹ ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሳሉ አርነት ወጥተናል

(ወደ ገጽ 3 ይዞራል)

# አምላካዊ መልስ ምን አለ?

«ለበኣል ያልሰገዱትን ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀርቼአለሁ» /ሮሜ.11፡41፣ ነገሥ.19፡18/

ይህ አምላካዊ መልስ የተገለጠው በዘመነ አክዓብ በእስራኤል ትንቢት ይናገር ለነበረው ለነቢዩ ኤልያስ ነበር። ኤልያስ በግል ማንነቱ ብዙም ዝናኛ ያልነበረ ሰው ነው። በሰዎች ዘንድም የተከበረ አልነበረም። መጽሐፍ ቅዱስ ኤልያስ በገለዓድ የነበረችው የቴስቢ ሰው እንደነበረ ይገልጻል /1ነገሥ.17፡1/፤ ገለዓድ ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ ከገሊላ ባሕር በስተደቡብ የምትገኛ ወረዳ ናት። ቴስብያዊው ኤልያስ በዘመኑ ብዙም ታዋቂነት ባይኖረውም ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀናኢ ነበረ።

ኤልያስ ለነቢይነት አገልግሎት የተጠራበት ዘመን በእስራኤል ምድር አምልኮተ እግዚአብሔር የተናቀበት፣ የእግዚአብሔር ስምና ክብር የተደፈረበት ዘመን ነበር፤ በአምልኮተ እግዚአብሔር ፈንታም አምልኮተ ጣኦት የነገሠበት፣ ልማደ አሕዛብ የተስፋፋበት ሁኔታ በእስራኤል ምድር ላይ ይታይ ነበር። የ10ሩ ነገድ መንግሥት በሆነው በእስራኤል መንግሥት ውስጥ የነገሡት አብዛኞቹ ነገሥታት በእግዚአብሐር ፊት ክፉ በማድረግ የሚታወቁ ነበሩ፤ የብዙዎቹም ክፋት በእስራኤል መንግሥት /በ10ሩ ነገድ/ ውስጥ

(ወደ ገጽ 2 ይዞራል

# እውነት

**በየሁለት ወሩ የሚወጣ የክርስቲያኖች ጋዜጣ**

**ዋና አዘጋጅ፤** **መዘምር በለጠ**
**ም/ዋና አዘጋጅ፤** **ደጉ ምሕረቴ**

## መልእክተ እውነት

**ይድረስ ለአንባብያን**

ማናቸውም ጽሑፍ ከመነበቡ አስቀድም ወይም ሲነበብ በአንባቢው አእምሮ ከሚነሱ ጥያቄዎች ውስጥ ዋንኛው የጸሐፊው ማንነት ነው:: «እውነት» ጋዜጣንም ስታነቡ አሳታሚው ማነው? ዓላማውስ ምንድነው? እንዴትስ በነፃ ሊደርሰኛ ቻለ? የሚል እንደሚሆን ከወዲሁ መገመት ይቻላል:: የእውነት ጋዜጣ ተልዕኮ አንድ ብቻ ነው፤ ይኸውም የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ለሰው ሁሉ ማድረስ ነው:: አሳታሚው ከዚህ በፊትም መንፈሳዊ መጻሕፍትን እያሳተመ በነጻ ለአንባብያን የሚያቀርብ ሲሆን ከመጻሕፍት ዝግጅት ሌላ የጋዜጣ ዝግጅት እንዲኖር ከአንባቢያን ከሚቀርቡ ጥያቄዎች በመነሣት የእግዚአብሔርን ቃል ከፊት ይልቅ በሰፊው ለማድረስ «እውነት» ጋዜጣ ለንባብ እንድትበ ሆኗል::

የእውነት ባለቤቷ እውነተኛው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ሁሉ «እውነት» ጋዜጣም ፍጹም እውነተኛ ለሆነው እግዚአብሔር ወገናዊነትን ከማሳየት በቀር ከየትኛውም የሃይማኖት ድርጅት ከመወገን የራቀች ናት:: በነፃ የምትታደለውን ያህል ከማናቸውም የሃይማኖት ጎራ አስተሳሰብ ነጻ ናት:: ከሕያው እግዚአብሔር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ከመንፈስ ቅዱስም ሌላ ማንንም ደስ የማሰኘት ዕቅድ የላትም፤ የሐሰትን ሐሰተኛነት ከመግለጥ ባሻገር ማንንም ለይቶ የመንቀፍ ዓላማም የላትም:: «እውነት» ጋዜጣ የእውነት ማህደር እንደመሆኗ መጠን «ዓመፃን ሁሉ ትጠላለች፤ ጽድቅን ሁሉ ትወዳለች» የጽድቅ ወዳጅ የዓመፃ ጠላት ናት:: ማንም ይሁን ምንም፣ የትም ይኑሩ የት፣ ከእውነተኞች ጋር ደስ ይላታል፤ የዓመፅ አስተሳሰብን ግን በጽኑዕ ትዎማለች:: እግዚአብሔር የሚጠላውን ሐሳብ ትጠላለች፤ እግዚአብሐር የሚወደውን ትወዳለች:: አንባቢዎቿንም «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዓመፅ ይራቅ» /2ጢሞ2፡19/ የሚለውን ታስተምራለች እንጂ ከዚህ የሃይማኖት ድርጅት ወጥታችሁ ከዚያኛው ግቡ አትልም:: ማንንም ቢሆን ሰውን ለማዳን ወደ ተገለጠ ወደ እግዚአብሔር ልጅ እንጂ ወደ የትኛውም በሰው ወደ ተዋቀረ ሥርዓት አትጠራም:: በሚጠሏትም ቢነገር ከእውነት ጋር ደስ ይላታል::

እውነት ጋዜጣን ለማሳተምም ሆነ ለማሰራጨት የሚያስፈልግ ገንዘብ የሚገኘው ከእውነት ወዳጆች ነው:: «በከንቱ ተቀበላችሁ፤ በከንቱ ስጡ» /ማቴ10፡8/ በተባለው መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ስጦታን በከንቱ /በነጻ/ እንደተቀበሉ ለሚያውቁና በከንቱ ለመስጠት በተዘጋጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች የገንዘብ፣ የጉልበት፣ የአእምሮ አስተዋጽዖ የምትደገፍ ናት::

የወንጌልን እውነት በጽሑፍ ቢደርሳቸው በተረጋጋ መንፈስ ሆነው በልበ ሰፊነት እየመረመሩ ወደ ጽድቅ መንገድ መመለስ የሚችሉ ሰዎች እያሉ የመግዛት አቅም በማጣት ብቻ ያልቻሉ ብዙ ሰዎች አሉ፤ ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች እውነትን ማዳረስ የአሳታሚው ዋና ዓላማ በመሆኑ ጋዜጣዋ በነጻ ልትታደል ችላለች:: ለእግዚአብሔርና ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ወገን የሆኑ ሁሉ ባላቸው ነገር ቢሳተፉባት በእጅጉ ይደገፋል::

ከዚህም በላይ አንባብያን ሁሉ «እውነትን» አንብበው ላላነበቡአት ሰዎች አሳልፈው እንዲሰጡ በእግዚአብሔር ርኅራኄ ይለመናሉ:: ይህንንም በማድረጋቸው የእግዚአብሔርን እውነት በማሰራጨት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ሊሰማቸው ይገባል፤ ጋዜጣዋን ካነበቡ በኋላ ሌሎች ሳያነቡአት እንድትቀመጥ ማድረግ የያዘችው የእውነት ምስክርነት እንዲሮጥ ያለብንን ኃላፊነት መዘንጋት ነው:: ስለሆነም እውነት ጋዜጣ የምትመሰክረውን እውነት ለሌሎች በማዳረስ ለኀሊናቸው የሚሰማቸውን ክርስቲያናዊ ኃላፊነት እንዲፈጽሙ ለአንባቢያን መልእክታችንን እናስተላልፋለን::

*«ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከዘላለም ድረስ ክብር ይሁን አሜን» /ሮሜ 16፡27/::*

## አምላካዊ መልስ.... ከገጽ 1 የዞረ

የመጀመሪያው ንጉሥ በነበረው በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄዳቸው ነበር፤ የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም 10ሩን ነገድ ከፍሎ በእነርሱ ላይ በነገሠ ጊዜ የግል ሥልጣኑንና ክብሩን ለማስጠበቅ ሲል እንዲሰገድላቸው ሁለት የወርቅ ጥጆችን አቁሞ «እስራኤል ሆይ ወደ ኢየሩሳሌም ትወጡ ዘንድ ይበዛባችኋል፤ ከግብፅ ምድር ያወጡህን አማልክትህን እይ» ብሎ ነበር:: ይህም ህዝቡ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለመሠዋት ብሎ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድና ልቡም በይሁዳ መንግሥት እንዳይከፈል ለመከላከል የተጠቀመበት ዘዴ ነው:: ይሁን እንጂ ይህ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ሆነ /1ነገሥ.12፡25-30/:: ከእርሱ በኋላ የተነሡት ነገሥታትም በእርሱ የኃጢአት መንገድ እየሄዱ የእስራኤልን አምላክ ያስቈጡ ነበር /1ነገሥ.15፡25 -26፣34 ፤ 16፡7፣19፣26/:: ነገር ግን በኤልያስ ዘመን የነበረውና ሰባተኛው የእስራኤል ንጉሥ የሆነው አክዓብ የሠራው ክፋት ከሁሉም የሚበልጥ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጥ «የዘንበሪም ልጅ አክዓብ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ፤ በናባጥም ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄድ ታናሽ ነገር መሰለው፤ የሲዶናውያንንም ንጉሥ የኤትበኣልን ልጅ ኤልዛቤልን አገባ ሄዶም በኣልን አመለከ፤ ሰገደለትም:: በሰማርያም በሠራው በበኣል ቤት ውስጥ ለበኣል መሠዊያ አቆመ:: አክዓብም የማምለኪያ አፀድ ተከለ፤ አክዓብም ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን የሚያስቈጣውን ነገር አበዛ» ይላል /1ነገሥ.16፡30-33/:: የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ያቆማቸውን ሁለት ጥጆች ማምለክና ማስመለክ ለአክዓብ ታናሽ ነገር ስለመሰለው በሲዶና አገር ይመለክ የነበረውን የበኣልን አምልኮ ወደ እስራኤል ምድር አስገባ:: በዚህም የረከሰ አምልኮ የእስራኤልን ሕዝብ አሳተ /1ነገሥ.16፡18/:: ሚስቱም ኤልዛቤል ይህን ክፉ ድርጊቱን እንዳይወሙበት በመፈለግ ስለ እግዚአብሔር ስምና ክብር የሚቈረቈሩ ነቢያተ እግዚአብሔርን ታስገድል ነበር/1ነገሥ.18፡4/፤450 የበኣል ነቢያትም ነበሯት/1ነገሥ 18፤19/::

ይህ ኤልያስ በነበረበት ዘመን ያለው የእስራኤል ሕዝብ መንፈሳዊ ድቀት ባለንበት ዘመን ካለውና በስመ ክርስትና ከሚጠራው ዓለም መንፈሳዊ ውድቀት ጋር በእጅጉ ተመሣሣይነት አለው:: እስራኤል ከግብፅ ምድር ያወጣቸው አምላክ ያደረገላቸውን ሥራ ሁሉ ለወርቅ ጥጆች በመስጠት በናባጥ ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት እንደሳቱ ሁሉ ዛሬም ከኃጢአትና ከሞት ባርነት ነጻ

*(ወደ ገጽ 4 ይዞራል)*

# አገልግሎት



የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ/ዮሐ12.፡26/

## «የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነው»
**ቈላ.** 3፡24

ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ የተነገረው ዘመኑ በፈጠረው ማህበራዊ ቀውስ የተነሣ በባርነት ቀንበር ተይዘው ለነበሩ አማኞች ነው፣ ምንም እንኳን ባሪያዎች ሆነው ለሰው የሚያገለግሉ ቢሆኑም ሐዋርያው ለእነዚህ አማኞች «በቅን ልብ ጌታን እየፈራችሁ እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ ሳትሆኑ በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ በሁሉ ታዘዙ፣ ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት፣ ከጌታ የርስትን ብድራት እንድትቀበሉ ታውቃችሁና፣ <u>የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነውና</u>» በማለት ጻፈላቸው /ቈላ3፡22-24/፡፡ ይህም አማኝ የሚያደርገውን ሁሉ ስለክርስቶስ ብሎ ቢያደርገው የርስትን ብድራት እንደሚቀበል ከመግለጡም ሌላ አንድ ሰው ስለ ጌታ ብሎ የሚሠራው ማናቸውም ሥራ ሁሉ ለጌታ ብሎ እስከሠራው ድረስ አገልግሎት መሆኑን ያስረዳል፡፡ በሥጋ አሠሪዎቻችን ለሆኑ ሰዎች የምንሠራው ሥራ የጌታ አገልግሎት ከሆነና ስለዚህም ሲባል በትጋት መሠራት ካለበት በቀጥታ ለእርሱ የሚሰጠው የወንጌል አገልግሎት ደግሞ ምንኛ የሚበልጥ የርስት ብድራትን ያሰጥ! አማኝ ባሪያ በሥጋ ጌታ ለሆነለት ሰው በትጋት የሚሠራው አገልግሎት ጌታ ክርስቶስን ማገልገል ከሆነ ስለጌታ ብለው ወንጌልን ማገልገል ደግሞ ይበልጡኑ ጌታ ክርስቶስን ማገልገል እንደምን አይሆንም? በእርግጥ ሰው ጌታን የሚያገለግለው በወንጌል ሥራ ብቻ አይደለም፣ ማናቸውንም አግባብነት ያለውን ኃላፊነት ስለጌታ ብሎ በታማኝነት መወጣት በራሱ አገልግሎት መሆኑን ይህ ንባብ በግልጥ ያሳያል፡፡ ሰው ስለጌታ ብሎ በሥራው ላይ ቢ ታመን፣ የተጣለበትን ግዴታ ቢወጣ ይህ አድራጎቱ ጌታን ማገልገል ነው፡፡ ወንጌልን የሚያገለግሉ ደግሞ ይበል ጡኑ የሚያገለግሉት ጌታ «ክርስቶስ» መሆኑን ሊረዱ ይገባቸዋል፡፡ ስለሆነም ስለ ወንጌል አገልግሎት ምንነትና ጠባይ በስፋት ከመነጋገራችን በፊት መገንዘብ ያለብን የምናገለግለው ማንን ነው? የሚል መሆን ይኖርበታል፣ ምክንያቱም የሚያገለግሉትን ለይቶ አለማወቅ አገለግሎቱን ባለቤት የሌለው ያደርገዋልና፣ አገለግሎቱ ባለቤት የሌለው ከሆነ ደግሞ ብድራት የለውም ማለት ነው፣ ይህ ደግሞ አገልጋዩን ከንቱ ያደርገዋል፣ አገልግሎቱም አገልግሎት ሊሰኝ አይችልም፡፡ የእውነተኛ ክርስቲያን አገልግሎት ባለቤት «ጌታ ክርስቶስ» ሲሆን እርሱም ለታማኝ አገልጋዮቹ ብድራትን ያውም አክሊልን ይሰጣቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ምንም ያህል በቀና አመለካከት ቢጀመርም አንድ አገልግሎት የጌታ አገልግሎት የማይሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ አገልግሎት በበጎና በቀና ሐሳብ የተጀመረ ቢሆንም የእግዚአብሔርን ፈድ የተከተለ ካልሆነ አገልገሎቱ የጌታ ላይሆን ይችላልና፣ በጎ የሆነ አገልግሎት ሁሉ የእግዚአብሔር ፈድ ላይኖረው ይችላል፣ ስለሆነም በአገልግሎታችን ውስጥ ቀዳሚ ሊሆን የሚገባው ለእግዚአብሔር ፈድ መገዛት ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ቤተመቅደስን በኢየሩሳሌም መሥራት በዳዊትም ሆነ በነቢዩ ናታን ፊት በጎና የተቀደሰ ሐሳብ ሆኖ ነበር፣ ሆኖም ይህ መልካም ሐሳብ የሰው ሐሳብ ነበር እንጂ የእግዚአብሔር ሐሳብ አልነበረምና ዳዊት ያሰበውን እንዳይሠራ ተከለከለ /2ሳሙ.7፡1-6/፡፡ ይህም

*(ወደ ገጽ 12 ይዞራል)*

## እውነት አርነት..ከገጽ 1 የዞረ

የሚሉና ለሌላውም አርነትን የሚሰብኩ ናቸው፣ እንደእነዚህ ዓይነት ሰዎች «እውነት አርነት ያወጣችኋል» የሚለውን የኢየሱስን ትምህርት በእልከኛ ልብ ሳይወሙ ወደማስተዋል ተመልሰው ቢሰሙት መልካም ይሆንላቸዋል፡፡

ባሁኑ ጊዜ በተለያዩ አስተምህሮዎች የሚመሩ የተለያዩ የእምነት ጎራዎች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ ባንድ ጎራ ውስጥ ያሉት በሌላው ያሉትን በባርነት እንዳሉ በማሰብ አንዳቸው ሌሎቹን አርነት ለማውጣት የየበኩላቸውን ጥረት የሚያደርጉባቸው በሥጋ ጥበብ የተሞሉ አገልግሎቶች ይታያሉ፣ ሁሉም ግን ራሳቸው የተያዙበትን የጥፋት ባርነት ሊያስተውሉ አልቻሉም፣ «ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው አርነት ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጡአችኋል» እንደተባሉት ዓይነት ሰዎች ሆነዋል /2ጴጥ.2፡19/፣ እንደ እነዚህ አይነት ሰዎች ሌሎችን አርነት እናወጣለን በሚል ሰበብ በባርነት ሠፈር ውስጥ ሲኖሩ እናያለን፡፡ ትክክለኛ ምክንያታቸውን በቅርበት ስንመረምረው ግን በዚያ የባርነት ሠፈር ውስጥ የሚገኙት ሌሎችን አርነት ለማውጣት ሳይሆን መልኩን በቀየረ በሌላ ዓይነት ባርነት ስለተያዙ እንደኾነና ሌሎችንም ወደዚያው ባርነት ለመክተት እንደሆነ እናስተውላለን፡፡ እንደእነዚህ ያሉ ሰዎች ይህን የሚያደርጉት ምናልባትም የእውነትን ቃል በግልጥነት ቢናገሩ የሚደርስባቸውን ነቀፋና መከራ ከመፍራት ሊሆን ይችላል፣ ወይም ከቤተሰብና ከማኅበራዊ ኑሮ ላለመገለል የሚጠቀሙበት ዘዴ ሆኖ ይገኛል፣ ካልሆነም ደግሞ የወንጌልን አገልግሎት

*(ወደ ገጽ 8 ይዞራል)*

## አምላካዊ መልስ... ከገጽ 2 የዞረ

ያወጣንን የኢየሱስ ክርስቶስን የማዳን ሥራ ለፍጡራንና ለቅርፃ ቅርፆች ወይም በምትካቸው ለቆሙና የሥጋ አእምሮ ውጤቶች ለሆኑ የሰው ሥርዓቶች ወይም ለምናባዊያን/የሐሳብ/ ጣኦታት እየሰጠ ብዙዎችን የሚያስተው የክፉው ምክር በእጅጉ በሠለጠነበት ዘመን ላይ እንገኛለን።

ዓለማዊ ጠባይን በተላበሱት መለካውያን አብያተክርስቲያናት ሁሉ የእግዚአብሔርን ሥራና ክብር የወሰዱ ወይም የሚጋሩ የተለያዩ ከቁሳቁስ የተሠሩ ወይም የሐሳብ ጥጆች መኖራቸው ግልጽ ነው። የአክዓብ መንፈስ ደግሞ ይህም ታናሽ በደል ሆኖበት የኤልዛቤልን መንፈስ ማለትም አምልኮተ አሕዛብን ወደ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በማስገባት አሁንም በመሥራት ላይ ይገኛል። የቀደመው የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ይዘት ወደጐን ተትቶ በአብያተክርስቲያናት ስም የሚጠራው ማኅበረሰብ በልማደ አሕዛብ ተጽዕኖ ሥር ወድቆ ስንመለከት ከልብ ልናዝን ይገባል። እንደ ኤልያስም በታላቅ መንፈሳዊ ቅንዓት ተነሣስተን ለእግዚአብሔር እውነት እና ለእግዚአብሔር አምልኮ ልንቆም ያስፈልጋል።

«በኣል» የተባለው ጣኦት በሲዶናም ሆነ በሚመለክባቸው በሌሎች ቦታዎች ሁሉ ዝናብንና ለምድርም ፍሬን የሚሰጥ የእርሻ አምላክ ተደርጐ የሚታሰብ ጣዖት ነበር። ይሁን እንጂ ዝናብን የሚያዘንብ ፀሐይን የሚያወጣ ለምድርም ፍሬን የሚሰጥ እግዚአብሔር ብቻ ነው/ዘዳ.11:13-17፤ ማቴ.5:45/። ይህንን እውነት በመጋፋት እስራኤል በየስፍራው ብዙ የበኣል ጣዖታትን /በኣሊምን/ በማቆም እግዚአብሔርን ቢያስቀኑትም በነቢዩ በኤልያስ በኩል በተነገረው የትንቢት ቃል መሠረት በኣል እግዚአብሔር የዘጋውን ሰማይ ሊከፍት የማይችል ባዶ ምስል ብቻ እንደሆነ ታወቀ፤ የእግዚአብሔር ነቢይ ኤልያስ ለእግዚአብሔር እጅግ በመቅናት «በፊቱ የቆምኩት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን ከአፌ ቃል በቀር በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም» ብሎ ለአክዓብ ተናገረው/1ነገሥ.17፤1/። ለ3 ዓመት ከ6 ወር ያህል ዝናብ ሳይዘንብ በመቅረቱ በእስራኤል ብቻ ሳይሆን ራሱ በኣል በኖረበት አገር በሲዶናም ጭምር ረሀብ ሆነ/ያዕ.5:17፤ 1ነገሥ.17:7-12/፤ ይህም ክስተት «ዝናብን ይሰጠናል፤ እርሻችንንም ያሰምርልናል» ብለው በተከተሉት ሁሉ ዘንድ በኣልን ከታላቅ ውርደት ላይ የጣለው የእግዚአብሔር ክንድ ነበር። ዛሬም በተለያዩ ምድራዊ ምክንያቶች እያታለለ የሕዝቡን ልብ የያዘው ክፉ መንፈስ የእግዚአብሔር ክንድ ሲገለጥበት በታላቅ ዕፍረትና መዋረድ እንደሚወገድ እርግጥ ነው።

ኤልያስ የአክዓብንና የኤልዛቤልን ክፋት ፊት ለፊት መቃወሙ በዚህ ዘመን ላሉት የእግዚአብሔር ልጆች ታላቅ መልእክትን ይሰጣል። ኤልያስ በረሀቡ ዘመን ማብቂያ ላይ ለአክዓብ ተገለጠ፤ ከዚያም በኣልን ከሚያገለግሉት ነቢያትና ካህናት ጋር ፊት ለፊት ገጥሞ በእግዚአብሔር ጉልበት በመታመን ከተገዳደራቸው በኋላ አሳፋሪ ሽንፈታቸው በሕዝብ ፊት እንዲገለጥ በማድረግ ኤልዛቤል ከባዕድ ምድር ያመጣችው አምልኮ በእስራኤል ፊት የተናቀ እንዲሆን አድርጓል /1ነገሥ18:16-40/። ይህ ኤልዛቤልን እጅግ ሊስቆጣትና እርምጃም ለመውሰድ ሊያነሣሣት የሚችል ጉዳይ እንደሆነ ቢታወቅም ከእርሷ የንግሥትነት ሥልጣን ይልቅ በሁሉ ላይ በቅን የሚፈርደው የነገሥታት ንጉሥ እግዚአብሔር እርሱ ታላቅ አምላክ መሆኑ ግልጽ ነው።

### ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ አለኝ

በዘመናችን በስመ ክርስትና በሚጠራው ዓለም ውስጥ በማታለል እየሠራ ያለውን የኤልዛቤልን መንፈስ በእግዚአብሔር ጉልበት ፊት ለፊት እንወመው ዘንድ በኤልያስ ልብ ልንነሣሣ ይገባናል፤ የዘመናችን ዓለማዊት ቤተክርስቲያን በመካከሏ ካለው የኤልዛቤል መንፈስ ጋር ተስማምታ መኖርን ብትመርጥም እግዚአብሔር ግን ጉዳዩን በቸልታ የሚመለከተው አይደለም። የከበረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለትያጥሮን ቤተክርስቲያን በተናገረው መልእክት ውስጥ «ሥራህንና ፍቅርህን እምነትህንም አገልግሎትህንም ትዕግሥትህንም ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው እንዲበዛ አውቃለሁ። ዳሩ ግን ነቢይ ነኝ የምትለውን ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተምረውንና የምታስተውን ያቺን ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ» ብሎ ሲናገር እንሰማዋለን /ራእ2:19-20/። በእርግጥ የዘመናችን ኤልዛቤል ሴሰኛነትንና አምልኮተ ጣዖትን በግልጥ ላትሰብክ ትችላለች፤ ምእመናን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያውቁበትና ወንጌልን የሚሰሙበት ብዙ ዕድል ስላለ በቀላሉ ሊስቱላት እንደማይችሉ ስለምታውቅ ልዩ የማታለል ባሕርይ መላበስን መርጣለች። የተቀደሱ የክርስትና አመለካከቶችን የተላበሱ ሥርዓታትን ፈጥራ ወይም ጌታ ታላላቅ ሥራዎችን የሠራባቸውን ቀናትና ቦታዎች በአል በማለት አዳኛና መድኃኒት አድርጋ በክርስቶስ ፈንታ ታቆማለች፤ የጌታንም ስም ብትጠራ በጌታ ፈንታ የተካቻቸውን ሥርዓቶች የተቀደሱ ለማስመሰል እንጂ ጌታን ለማክበር አይደለም። «ነቢይ ነኝ፣ ራእይ ታይቶኛል፣ እግዚአብሔር ልኮኛል» በማለት በእግዚአብሔር ስም በሕዝብ ፊት እየቀረቡ የሕዝቡን ልብ በወግና በሥርዓት የሚይዙ፣ እንዲሁም «በመገለጥ ታይቶኛል፣ ጌታ ተናግሮኛል፣ የተቀባሁ አገልጋይ ነኝ» እያሉ የብዙዎች ልብ ስለገንዘብና ስለትዳር በማሰብ እንዲከብድ የሚያደርጉ፣ የኤልዛቤል አገልጋዮች በቤተክርስቲያን ውስጥ ተሰግስገው እየታየና በመንፈስ ቅዱስ ስምም የውሸት ልን እንደሚናገሩ በትክክል እየታወቀ በቸልታ መታለፋቸው የከበረውን ኢየሱስን በእጅጉ ያሳዝነዋል። ከዚህም ሌላ «ህልም ታይቶኛል፤ መልእክ ተገልጦልኛል» በማለት ምንጭ ፈልገው አጥማቂ የሚሆኑ፣ አጋንንትን የሚያስጎሩ እንጂ የማያወጡ፣ የነፍሳትን አእምሮ ከጌታ መስቀል ወደ ኮረብቶችና ምንጮች የሚያዞሩ የኤልዛቤል መልእክተኞች እንደ ቅዱሳን ተቈጥረው ሲታለፉ የኤልያስ አምላክ ምንኛ ያዝን ይሆን? ምክንያቱም ይህ የኤልዛቤል አገልግሎት ሕዝቡን በቀጥተኛ መንገድ ባይሆንም በተዘዋዋሪ መንገድ ወደ ሚፈጸም ባዕድ አምልኮ የሚመራ የክፋት አሠራር ነውና። ስለዚህም እንደ ኤልያስ በቀናዒነት የሚያገለግሉ የወንጌል መልእክተኞች ኤልዛቤልን በጥብቅ ሊወጧት ይገባል። ወይም በቸልታ የሚያዩአት ከሆነ ግን የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ እያንዳንዳቸውን «ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ» ይላቸዋል።

### ለኤልያስ ክስ የመጣው አምላካዊ መልስ

ኤልያስ ለሠራዊት አምላክ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቶ በእግዚአብሔር ጉልበት ባደረገው ተጋድሎ በበአልና በነቢያቱ ላይ የተቀዳጀው ድል ኤልዛቤልን በእጅጉ አበሳጫት፣ ልትገድለውም በአማልክቷ ስም እየማለች ዛተችበት/ነገሥ.19:2/። ኤልያስ ለግድያ እንደሚፈልግ ባወቀ ጊዜ ፈርቶ ተሰደደ። በይሁዳ ከሚገኘው ከቤርሳቤህ በኋላ የአንድ ቀን መንገድ ሄዶ ከክትክታ ዛፍ በታች ተቀመጠና በእግዚአብሔር ፊት ተማረረ፤ በዚያም «ይበቃኛል አሁንም አቤቱ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ ብሎ እንዲሞት ለመነ» /1ነገሥ.19:4/

*(ወደ ገጽ 6 ይዞራል)*

ኀበ ሀለዉ ክልኤቱ ወሠለስቱ ጉቡኣን **በስምየ** ህየ ሀለውኩ አነ ማዕከሎሙ /ማቴ18፡20/

ቤተክርስቲያን



ሁለት ወይም ሦስት **በስሜ** በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ /ማቴ18፡20/

# ቤተክርስቲያን በማቴዎስ ምዕ.16

በክርስትና ስም በሚጠራው ዓለም ሆነ ክርስቲያን ባልሆነው ዓለም «ቤተክርስቲያንን» በተመለከተ ያለው መረዳት መጽሐፍ ቅዱስ ከሚነግረን እውነት ጋር በሚፋለስበት በዚህ ዘመን ስለ ቤተክርስቲያን ያለውን ትክክለኛ ሐሳብ ማወቅ በብዙዎች ዘንድ የሚናፈቅ ሆኗል:: በብዙ የዶክትሪን አስተሳሰቦች እና ሥርዓተ አምልኮዎች የሚለያዩና በተለያዩ ስያሜዎች የሚጠሩ አብያተ ክርስቲያናት በበዙበት በዚህ በያዝንው ክፍለዘመን የቤተክርስቲያንን ትክክለኛ ማንነት ለማወቅ የተጠማውን የሰዎችን ኅሊና የሚያረካ እውነት መገኘት የሚችለው ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ከተጻፈው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብቻ ነው:: ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወደ 150 ጊዜ ያህል ተጠቅሶ የሚገኝ በመሆኑ የቤተክርስቲያን ትክክለኛ ገጽታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስፋት ይገኛል፣ የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነት በውስጥ ጆሮአችን እያዳመጥን ብናነበው ስለ ቤተክርስቲያንም ሆነ ስለሌሎች ታላላቅ መንፈሳውያን ርእሶች የተገለጠ እውነትን እናገኝበታለን::

## የቤተክርስቲያን እውነተኛ ማንነቷ

«ቤተክርስቲያን» የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ «ኤክሌሲያ» ለሚለው ቃል የተሰጠ ትርጉም ሲሆን ኤክሌስያ ማለትም «የተጠራች ጉባዔ» ማለት ነው:: በግእዝም ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል የክርስቲያን ቤት የሚል ፊደላዊ ፍቺ ቢኖረውም ዋነኛ ሐሳቡ «የክርስቲያን ወገን» ማለት ስለሆነ ኤክሌስያ የሚሰጠንን ስሜት በተወሰነ ደረጃ ይዟል፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን በምድር ላይ የነበረችው በእግዚአብሔር የተመረጠች ጉባዔ ቤተእስራኤል ነበረች:: ይህችም ጉባዔ ማለትም እስራኤል፣ ኤክሌሲያ ተብላ የተጠራችበትን የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እናገኛለን/የሐ.ሥ.7፡38/:: በሌላ በኩል ደግሞ በአሕዛብ አገርም በአንድ ምክንያት የሚሰበሰብ ትልቅ ጉባዔ ኤክሌስያ ይባል ነበር/የሐ.ሥ19፡3/:: እነዚህ በቤተ እስራኤልም ሆነ በቤተ አሕዛብ የነበሩት ጉባዔያት ምድራውያን ሲሆኑ በወንጌል ቃል በኩል ከዚህ ዓለም የተጠሩት ክርስቲያኖች ጉባዔ /ኤክሌስያ/ ግን ሰማያዊ ባሕርይ ያላት ጉባዔ ናት፣ ሐዋርያው ጳውሎስ «...ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን <u>በቤተክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ</u> ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ...»/ኤፌ3፡10/ ብሎ ከጻፈው ቃል ውስጥ ይህንን የቤተክርስቲያንን ሰማያዊ ባሕርይ እንረዳለን:: በብሉይ ኪዳን የነበረችው የተጠራች የእግዚአብሔር ጉባዔ በሥጋ ከአብርሃም ዘር የሆኑትን ብቻ ያካተተች ጉባዔ ነበረች:: በአዲስ ኪዳን ያለችው የእግዚአብሔር ጉባዔ (ኤክሌስያ) ግን ከቤተ እስራኤል ብቻ ሳይሆን ከቤተ አሕዛብም የሆኑትን ወገኖች ያቀፈች ጉባዔ ናት:: በዘመነ አበው እግዚአብሔር «የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» /ዘፍ12፡32/ «በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ ዘርህንም እንደሰማይ ከዋክብት በባሕር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ ሌን ሰምተሃልና» ብሎ ለአብርሃም አስቀድሞ የሰጠው የተስፋ ቃል የተፈጸመው በአዲስ ኪዳን ዘመን ነው/ገላ3፡8-16/:: መጥምቁ ዮሐንስ «ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆችን ሊያስነሣላቸው ይችላል» ብሎ «አብርሃም አባት አለን» እያሉ ለሚመኩት ፈሪሳውያን በተናገረው መሠረት/ማቴ3፤9/ ከቤተ አሕዛብ መካከል በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑ ሁሉ የአብርሃም ልጆች ለመሆን ችለዋል:: ጳውሎስም ክርስቶስ ኢየሱስ በእንጨት ላይ የተሰቀለው አሕዛብን በእርሱ በኩል ወደ አብርሃም በረከት ውስጥ ለማስገባት እንደሆነ ሲናገር «በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፏልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በእምነት ይደርስላቸው ዘንድ» ብሏል /በገላ3፡14/:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የመሠረተው ከቤተ እሥራኤልና ከቤተ አሕዛብ በተውጣጣ አዲስ ሕዝብ ነው:: በመስቀል ላይ የመሞቱም ዓላማ ይህንኑ አዲስ ሕዝብ ይፈጥር ዘንድ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጥ «እርሱ ሰላማችን ነውና ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአ ብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው» ይላል /ኤፌ2፡11-16/:: ከዚህም እንደምንረዳው በአዲስ ኪዳን ሰዎችን የእግዚአብሔር ህዝብ የሚያደረገው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው እንጂ እስራኤላዊ እና አሕዛባዊ የመሆን ጉዳይ አይደለም:: ስለዚህ የቤተክርስቲያን አባላት ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ድረስ ካሉት ነገዶች ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት ያመኑት ሁሉ ናቸው::

ይህም እውነት «ክርስቲያን መባል ያለብን እኛ ብቻ ነን ቤተክርስቲያንም የእኛ ቤተክርስቲያን ብቻ ናት፣ የክርስቲያን ደሴትም የእኛ ምድር ብቻ ናት» የሚለውን የተሳሳተ ብሂል የሚያርም የአዲስ ኪዳን እውነት ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ «በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና ለሚጠሩትም ባለ ጠጋ ነው፣ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና» የሚለው ቃል የገባቸውን ምእመናን በምድራቸውም ሆነ በሌሎች የውጭ አገሮች ውስጥ ሰዎች በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው መሰብሰባቸውን ይናፍሉ፣ እንዲህ ያሉት ምእመናን በዓለም ካሉት ነገዶች ሁሉ ሰዎች በክርስቶስ አምነው በስሙ የመሰባሰባቸውን ዜና ሲሰሙ ደስታና መንፈሳዊ ሐሴት ይሞላባቸዋል:: እንደዚሁም በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ እንደተመዘገበው የምስጋና ቃልም «መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሙንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፣ ታርደሃልና በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፣ በምድርም ላይ

*(ወደ ገጽ 8 ይዞራል)*

## አምላካዊ መልስ... ከገጽ 4 የዞረ

ለእግዚአብሔር አምልኮ በመቅናት በኤልያስ ስሜት ተነሣስተው የወንጌልን እውነት የሚገልጡ አገልጋዮች የኤልዛቤል መንፈስ ለሚያሰማቸው ዛቻ ጆሮ በሚሰጡ ጊዜ እንዲህ ያለ የስንፍና ቃልን ይናገራሉ:: «ብዙ አገለገልኩ፣ ብዙ ተጋደልኩ ከእኔ የሚጠበቀውን አድርጌአለሁ፣ ግን መከራው ከአቅሜ በላይ ሆነ አሁንስ በቃ ጌታ ሆይ ውሰደኝ» የሚሉ ቃላት ፈሪና ድንጉጥ ከሆነው ልባችን የሚወጡ የስንፍና ቃላት ናቸው:: በኢየሱስ ክርስቶስ ህይወት የሚኖር ቀናኢ አገልጋይ ግን «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ነገር ግን አይዟችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ» የሚለውን የኢየሱስን ቃል ሁል ጊዜም ያስባል /ዮሐ.16፡33/፤ እግዚአብሔርም አገልጋዩ ሥጋ ለባሽ እንደሆነ ያውቃልና በመከራ የተሰቀቀችውን የባሪያውን ነፍስ ለማረጋጋት በጸጋ አሠራሩ አይለየውም፤ ስለሆነም እግዚአብሔር ኤልያስን በመልአኩ በኩል ጎብኝቶት ነበር፤ እጅግ ደክሞት ከተኛበት ስፍራ በመልአክ ተቀስቅሶ ምግብ እንዲበላ ተደረገ፤ በዚያም ምግብ እስከ እግዚአብሔር ተራራ ድረስ 40 ቀንና 40 ሌሊት ሄደ /1ነገሥ19፡7-8/፤ በክርስትና ሕይወታችን በደከምንበት እና በጠወለግንበት ጊዜ ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር መግቦት ያስፈልገናል:: በእርግጥም እግዚአብሔር በፊቱ ለምንናገረው የስንፍና ንግግራችን አሳልፎ አይሰጠንም:: ኤልያስ እንዲሞት ቢለምንም እግዚአብሔር ግን እንዲኖር መገበው ፤ በተበሳጨን ቁጥር የምንጸልየውን ክፉ ጸሎት ሰምቶ አዎንታዊ መልስ የማይሰጥበት እግዚአብሔር ስሙ ቡሩክ ይሁን::

ኤልያስ በእግዚአብሔር መግቦት ከበረታ በኋላ በእግዚአብሔር ተራራ /ደብረ ሲና/ ሥር ባለ ዋሻ ውስጥ እናገኘዋለን:: በዚያም ሳለ «ኤልያስ ሆይ በዚህ ምን ታደርጋለህ?» የሚል የእግዚአብሔር ቃል መጣለት /ቁ.9/፤ በዚህ ጊዜ ነበር ኤልያስ እስራኤልን የሚከስ ቃል በእግዚአብሔር ፊት የተናገረው፤ እንዲህ በማለት፡ «ለሠራዊት አምላክ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ የእስራኤል ልጆች ቃል ኪዳንህን ትተዋልና፤ መሠዊያዎችህንም አፍርሰዋልና ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና እኔም ብቻዬን ቀርቻለሁ ነፍሴንም ሊወስዱአት ይሻሉ» /ነገሥ.19፡10/:: በሮሜ.11፡2 ላይ ይህ የኤልያስ ንግግር ክስ መሆኑ ተገልጧል፤ ምክንያቱም ይህ አባባሉ ከራሱ ይልቅ የሕዝቡን በደል የሚናገር በመሆኑ ነው::

ሁልጊዜም ተስፋ በቈረጠና በሚነጫነጭ ስሜት ውስጥ ያለ ክርስቲያን ከራሱ ይልቅ የሌሎች በደል ይታየዋል፤ በእርግጥ በሰው ሚዛን ሲመዘን ወይም በሰው ዓይን ሲታይ ከእኛ በቀር ለእግዚአብሔር የሚገዛ ልብ ያለው በምድር ላይ ፈጽሞ የሌለ ሊመስለን ይችላል:: ነገር ግን በስም ብቻ «ክርስቲያን» የሚባለውን ጨምሮ በምድር ላይ ያለው ሕዝብ በጥቅሉ የእግዚአብሔርን እውነትና የእግዚአብሔርን አምልኮ የሚጋፋ ነገር ሲያደርግ ብንመለከትም በእግዚአብሔር ዓይኖች ብቻ የሚታዩ ለስሙ የሚሆኑ ወገኖችም ሊኖሩ እንደሚችሉ ማሰብ ይገባናል:: ኤልያስ ይህንን ይማር ዘንድ አምላካዊ መልስ መጣለት:: ይህም አምላካዊ መልስ «...እኔም ከእስራኤል ጉልበታቸውን ለበኣል ያላንበረከኩትን ሁሉ፣ በአፋቸውም ያልሳሙትን ሁሉ፣ ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀራለሁ» የሚል ነው /1ነገሥ.19፡18/::

«እኔ ብቻ ቀርቻለሁ» በማለት ሲናገር ለነበረው ኤልያስ ይህ አምላካዊ መልስ አንገት የሚያስደፋና በተናገረው ነገር የሚያጸጽት ብርቱ ቃል ሆኖለታል:: «እኔ ብቻ» በማለት እኔነትን ለሚሰብኩና ለሚያወሩ ይህ አምላካዊ መልስ እንዴት ያለ ትምህርትን ይሰጣቸዋል!

### እንደዚሁም በአሁን ዘመን ደግሞ በጸጋ የተመረጡ ቅሬታዎች አሉ

በስመ ክርስትና የሚጠራው አለም በጥቅሉ በታላቅ መንፈሳዊ ውድቀት ውስጥ ቢገኝም እግዚአብሔር ግን ከዚህ መሐል ለስሙ የሚሆን ወገንን ለራሱ ያስቀራል:: በጢሞቴዎስ መልእክት እንደተጻፈው «ጌታ ለእርሱ የሆኑትን ያውቃል» /2ጢሞ.2፡19/፤ ወንጌል ለአይሁድም ለአሕዛብም እየተሰበከ በነበረበት በዘመነ ሐዋርያት የእግዚአብሔር ህዝብ ተብሎ የሚታወቀው ከአይሁድም ከአሕዛብም በኢየሱስ ያመነ ሕዝብ ነበር:: ይሁንና ከአይሁድ ካመኑት መካከል ብዙዎቹ «የእግዚአብሔር ሕዝብ እኛ ብቻ ነን» ብለው ለወንጌል እውነት አልሸነፍ አሉ፣ወደ ወንጌልም ከመጡ በኋላ ወደኋላ ያፈገፈጉ ነበሩ:: ከዚህ በኋላ ሐዋርያት ወደ አሕዛብ ዘወር ብለው ወንጌልን ስለሰበኩ ቤተክርስቲያን በአሕዛብ መካከል መስፋፋት ቀጠለች፣ ይህ ሲባል ግን እግዚአብሔር እስራኤልን ሙሉ በሙሉ ትቷቸዋል ማለት አልነበረም:: ይህንን ይረዱ ዘንድ በሮሜ ለሚገኙት ክርስቲያኖች ጳውሎስ መልእክትን ሲጽፍላቸው ለኤልያስ የተነገረውንና እግዚአብሔር ለራሱ የሚሆኑ ወገኖችን እንደሚያስቀር የሚናገረውን አምላካዊ መልስ በማስረጃነት በመጥቀስ እግዚአብሔር ህዝቡን እንደማይጥል ካስረዳቸው በኋላ «እንደዚህም በአሁን ዘመን በጸጋ የተመረጡ ቅሬታዎች አሉ» ይላቸዋል/ሮሜ11፡5/:: ዛሬ በዙሪያችን ያሉ መለካውያን አብያተ ክርስቲያናትን ጨምሮ ዓለሙ ሁሉ በክፉት አሠራር ተይዞ ስንመለከት ታድያ ከእኔ በቀር እግዚአብሔር ሌላ ምን ሰው አለው? ብለን በከንቱ እንዳንመጻደቅ ይህ ቃል በብርቱ ያሳስበናል::

ጌታ ኢየሱስ ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር ስለሆነ የእርሱ የሆኑትን ለይቶ ያውቃል /2ጢሞ2፡19/፤ በትያጥሮን ቤተክርስቲያን ውስጥ በኤልዛቤል አምልኮ ያልሳቱ ቅሬታዎች እንደነበሩባት ያውቅ ነበር /ራእ.2፡23/:: እንደዚሁም በዘመናችን በታላቅ መንፈሳዊ ውድቀት ውስጥ በሚገኙ አብያተክርስቲያናት ውስጥ ህዝብን በምታስተው በኤልዛቤል አሠራር ያልተያዙ የዋሃን አማኞችን ጌታ ለራሱ እንደሚያስቀር ልንረዳ ይገባናል:: እነዚህንም ከሚገኙበትና ባለማወቅ ከሚኖሩበት የማይታዘዝ ማኅበር ጌታ በጸጋው ለይቶ ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አንድ ቀን ያፈልሳቸዋል /ቈላ.1፡13፣ዕብ.13፡13/::

### እግዚአብሔር በኤልዛቤል ይፈርዳል

ኤልዛቤል ሲዶናዊት እንጂ እስራኤላዊት አልነበረችም፤ እስራኤላዊት አለመሆኗ ብቻ ሳይሆን የእስራኤልን አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን የምታምንና የምታመልክ አልነበረችም:: በተራኒው ግን የዚህን ሕያው አምላክ ክብሩንና አምልኮውን የሚጻፈር የረከሰ አምልኮ በእስራኤል ምድር ውስጥ እንዲሰለጥን ያደረገች ሴት ናት:: ከንጉሡ ከአክዓብ ጀምሮ እስራኤልን ሁሉ አሳተች፤ የእግዚአብሔርን ነቢያት ሁሉ በሰይፍ አስገደለች፣ በመጨረሻም ለእግዚአብሔር አምልኮ እጅግ ቀንቶ የነበረውን ነቢዩ ኤልያስን ልታስገድል አሳደደችው፣ እግዚአብሔር ይህ ሁሉ ሲሆን እያንደንዱን የኤልዛቤልን የክፋት እርምጃ በትዕግሥት ይመለከት ነበር:: ይሁንና ጊዜያቸውን ይጠብቁ እንጂ በእግዚአብሔር አምልኮ ላይ የተነሣሱ የክፋት አገልጋዮች እንዲህ በሥርዓተ አልበኞነትና በአረመኔያዊ ሥራቸው እንደሠለጠኑ አይቀጥሉም፤ ስለሆነም «በቀል የእኔ ነው እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ» ያለው ጌታ ኤልዛቤልን በፍርድ ሲበቀላት እንመለከታለን:: ኤልዛቤል ክፋቷ እያደገ መጥቶ ኢይዝራኤላዊውን ናቡቴን አስገድላ ርስቱን አክዓብ እንዲወርስ ባደረገች

*(ወደ ገጽ 9 ይዞራል)*

...በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ ታመልከው ዘንድ ...ነው እንጂ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚልፈገው ምንድር ነው? /ዘዳ. 10፡12/፡፡



# አምልኮት

እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን . . . ነንና /ፊልጵ.3፡3/

## ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ /ማቴ.4፡10፤ ሉ.4፡8/

በክርስትና ሕይወት ውስጥ ስለ አምልኮ ያለው ቀዳሚ እውነት «አምልኮ የሚገባው እውነተኛው አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው» የሚል ነው፡፡ በምድራችን ያለውን የአምልኮ ሕይወት ስንመለከት የእውነተኛውን አምላክ የእግዚ አብሔርን ህልውና የሚያውቁና ራሳቸውንም ክርስቲያን ብለው የሚጠሩ ነገር ግን የጥንቆላ፣ የአድባር፣ የጨሌ የቆሌ፣ የቦረንትቻ...አምልኮን አዳብለው የያዙ ብዙ ወገኖች ይኖራሉ፤ ከእነዚህም አንዳንዶቹ እነዚህን አምልኮዎች ከአምልኮተ እግዚ አብሔር ጋር ጐን ለጐን ይዞ መኖር እግዚአብሔርን የሚያሳዝነውና የሚያስቆጣው እንደሆነ እንኳ አያውቁም፤ ሌሎች ደግሞ ቅዱሳን መላእክትንና ቅዱሳን ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ደርበው ያመልካሉ፤ ሳይታወቻቸው /አምልኮ ሳይመስላቸው/ የእግዚአብሔር ለሆኑት ቅዱሳን የሚያቀርቡት አምልኮ ይበልጡኑ እግዚአብሔርን የሚያከብር ይመስላቸዋል፤ እንደዚሁም የእግዚአብሔርን የራሱን እና የቅዱሳኑን ምስሎች በሥዕልና በቅርፅ በማበጀት ለእነርሱ መስገድና ወደ እነርሱ መጸለይ እግዚአብሔርን የሚያስቀና ባዕድ አምልኮ መሆኑን ለመረዳት ለብዙዎች ገና አልተገለ ጠላቸውም፡፡

ሰይጣን በቀጥተኛ እና በተዘዋዋሪ መንገድ በክርስቲያኖች መካከል የሌሎች አማልክትን አምልኮ በማስገባት ብዙዎችን ተቈጣጥሮአል፤ ሆኖም በተለያዩ አማልክት ስም ይገለጥ እንጂ በሁሉም ዘንድ ባዕድ አምልኮን የሚቀበለውና የወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው የማያምኑትን ያሳወረው የዚህ ዓለም አምላክ የተባለው ራሱ ሰይጣን ነው /2ቆሮ.4፡4/፡፡ ሰይጣን ብዙዎችን ወደዚህ ባዕድ አምልኮ የሚስበው በዓለማዊ ክብርና ጥቅም ነው፡፡ ብዙዎች ሥራ ለመያዝ፣ ንግድን ትርፋማ ለማድረግ፣ ትዳርን ለማሳካት፣ ጠላትን ለመበቀልና ለማጥፋት፣ ከበሽታ ለመዳን፣ የወደፊት ዕድልን ለመወሰን...ወዘተ ግልጽና ስውር የሆኑ ባዕዳን አማልክትን ያመልካሉ፡፡ ሰይጣን በዚህ መልኩ አይናችንን ሊማርኩ የሚችሉ የዚህ አለምን ነገሮች እያሳየ እንድናመልከው ሲጋብዘን ጌታ ኢየሱስ የመለሰለትን ቁርጠኛ መልስ ልንመልስለት ይገባል፡፡ ጌታችን በምድረበዳ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ ሰይጣን ወደ ረጅም ተራራ ወስዶ «የዓለምን መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ ወድቀህ ብትሰግድልኛ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ» ብሎ ላቀረበለት ፈተና የሰጠው መልስ «ሂድ አንተ ሰይጣን፣ ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና፡፡» የሚል ነበር /ማቴ.4፡8-11/፤ «...እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና» በማለት ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀስን የሰይጣንን ሽንገላ በጥብቅ ልንዋም እንደሚገባን ከዚህ እንረዳለን፡፡ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ያሉት ቅዱሳት መጻሕፍት ከአንድ አምላክ ከእግዚአብሔር በቀር ሌሎች አማልክትን እንዳናመልክ በግልጽ ይነግሩናል፤ ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙት ጥቅሶች መካከል ከ10ሩ ቃላት የመጀመሪያው የሆነውን ቃል ብንመለከት «እግዚአብሔር ይህን ቃል እንዲህ ብሎ ተናገረ፡- ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚ አብሔር አምላክህ እኔ ነኛ፡፡ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» ይላል/ዘጸ.20፡1-3፤ዘዳ.5፡6-7/፡፡ እንደዚ ሁም በአዲስ ኪዳን ክፍል «... ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደሆነ ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃን» ይላል /1ቆሮ.8፡4/ በዚህ መልክ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ «ተብሎ ተጽፎአልና» ብለን ልንጠቅሳቸው የምንችላቸው ባዕድ አምልኮን የሚዋሙ ግልጽ ቃላት በብዛት ይገኛሉ፤ ለእግዚአብሔር ቃል ከልብ ብንገዛ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን አምልኮ በሙሉም ሆነ በግማሽ ለፍጡራን ወይም ለተቀረፁ ምስሎች ልንሰጥ አንችልም፡፡

በዓለማችን ውስጥ በተለይም በአሕዛብ ዘንድ አማልክት የሚባሉት በቁጥር ብዙ ናቸው፡፡ አንድ ሰው ብዙ አማልክትን ሊያመልክ ይችላል፡፡ ለምሣሌ ጎልያድ ዳዊትን እንደረገመው በተጻፈበት ክፍል «ፍልስጥኤማዊውም ዳዊትን በአምላኮቹ ስም ረገመው» የሚል ስናነብ/1ሳሙ.17፡43/ ኤልዛቤል በኤልያስ ላይ ያቀረበችውን ዛቻ በተመለከተ ደግሞ «...አማልክት ይህን ያድርጉብኛ ይህን ይጨምሩብኛ» እንዳለች እናነባለን /1ነገሥ.19፡2/፤ ይህም ለተለያዩ ጉዳዮቻቸው የተለያየ አማልክትን ከመፈለግ የመጣ ሊሆን ይችላል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክርለት አንድ አምላክ ግን በሁሉ ሥፍራ የሚገኛና ሁሉን መሥራት የሚችል ለማንኛውም የሰው ልጅ ጉዳይ የራሱ የሆነ ምላሽ ያለው አምላክ ነው፤ ይህንን በሚመለከት ሲናገርም «መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፣ ነገር ግን በሰማይ ሆነ በምድርም ሆነ አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ፣ ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ፣ እኛም ከእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን»ይላል /1ቆሮ.8፡5-6/፡፡ እንደዚሁም በሌላ ስፍራ ላይ «ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ» የሚል ቃን እናነባለን /ኤፌ.4፡5/፡፡ «ነገር ሁሉ በእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን፣ ከሁሉ በላይ የሚሆን፣ በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉም የሚኖር» የሚሉት እነዚህ ቅጽሎች ከአንድ ከሕያው አምላክ በቀር ለማንም ሊነገሩ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ሌሎች አማልክት የሚባሉት ሁሉ እንዲህ ያለ ብቃት የላቸውም፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አማልክት እየተባሉ የሚጠሩት የአሕዛብ አማልክት ብቻ ሳይሆኑ የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን ቅዱሳንም ናቸው፤ በመዝሙረ ዳዊት «እኔ ግን አማልክት ናችሁ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ» ተብሎ በተጻፈው ቃል ውስጥ አማልክት የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን እንደሚያመለክት ጌታ ኢየሱስ ተናግሯል/መዝ.81፡6፤ ዮሐ.10፡34-36/፡፡ ለምሣሌ እግዚአብሔር ሙሴን «እይ፡- እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ ወንድምህም አሮን ነቢይ ይሆንልሃል» እንዳለው እናነባለን፡፡ /ዘጸ.7፡1/ ከዚህ እንደምንረዳው እግዚአብሔር ቃሉን የሚሰጣቸው ባሪያዎቹን በክፉ ነገር ላይ አምላክ አድርጎ እየሾመ በአምላካዊ ሥልጣን ይልካል፡፡ ይሁን እንጂ እግዚ አብሔርን የሚያመልክ ህዝብ ለእነዚህ በአምላካዊ ሥልጣን ለተላኩት የእግዚ አብሔር ባሪያዎች እየሰገደና ወደ እነርሱም እየጸለየ እንዲሁም መሥዋዕትና እጣን፣ ከመዝሙር ጋር በማቅረብ እንዲያመልካቸው አላደረገም፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ እስራኤል ሙሴን በሕይወት እያለም

*(ወደ ገጽ 9ይዞራል)*

## ቤተክርስቲያን.. ..ከገጽ 5 የዞረ

ይነግሣሉ» እያሉ አዲስን ቅኔ በመዘመር ከ4ቱ እንስሶች እና ከ24ቱ ሽማግሌዎች /ሊናት/ ጋር በጉን /ጌታ ኢየሱስን/ ያመሰግኑታል /ራእ5፡9/፡፡

«ቤተክርስቲያን» የሚለው ቃል ከሕዝብና ከአሕዛብ መካከል እግዚአብሔር የጠራቸውንና የመረጣቸውን የአዲስ ኪዳን አማኞችን ኅብረት /ማኅበረ ምዕመናንን/ የሚያመለክት ሆኖ ሳለ ክርስቲያኖች ለመንፈሳዊ ጉዳዮች የምንሰበሰብበትን ቦታ ወይም አዳራሽ እንደዚሁም ራሳችን ስም አውጥተን የፈጠርነውን የእምነት ድርጅት እንዲያመለክት አድርገን መጠቀም የሉን ትርጉም ማዛባት ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ ኢየሱስ የሞተለትን አላማ ማስል ነው፡፡ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን የዋጃት በገዛ ደሙ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስረዳ «...በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ...» ይላል/የሐዋ.ሥራ20፡28/፡፡ ቤተክርስቲያን ህንፃ ወይም ድርጅት ከሆነች ደግሞ ክርስቶስ ለሕንፃ ወይም ለድርጅት ሞቷል ማለት ሊሆን ነው፤ ሆኖም በመጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል በሚገኛበት በማናቸውም ጥቅስ ውስጥ በምድር ላይ ሰማያዊ ባሕርይን ተላብሳ የምትገኘውን የተመረጠች የእግዚአብሔርን ጉባዔ ከማመልከት በቀር በአንድም ስፍራ ህንፃን ወይም ድርጅትን አያመለክትም፡፡ እንዲህ ሲባል ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ለማምለክና ሉን ለመስማት የሚሰባሰቡበት ቤት እንዲሁም እንደ የአገሩ ሕግ ለመሰብሰብ ሆነ ለሕዝብ መንፈሳዊ አገልግሎትን ለመስጠት የሚያስችላቸውን መንፈሳዊ ድርጅት ማቋቋም አይችሉም ማለት አይደለም፤ ይሁን እንጂ ህንፃውም «ህንፃ»፣ ድርጅቱም «ድርጅት» ሊባል ይችላል እንጂ «ቤተክርስቲያን» ሊባል አይችልም፡፡ ለምሳሌ በፊልሞና ቤት ውስጥ ትሰበሰብ ስለነበረችው ቤተክርስቲያን በፊልሞና መልእክት መግቢያ ላይ «በቤትህም ላለች ቤተክርስቲያን» የሚል ቃል እናነባለን/ፊል2/፡፡ በዚህ ንባብ ውስጥ ቤተክርስቲያን በፊልሞና ቤት ስለተሰበሰበች የፊልሞና ቤት ቤተክርስቲያን ተብላ እንዳልተጠራች እናያለን፤ በዚያ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ለቤተክርስቲያን መሰብሰቢያ ተብሎ ሕንፃ መሥራትም አልተጀመረም ነበር፡፡ ቤተክርስቲያን ትሰበሰብ የነበረው ከአማኞች መካከል ቤታቸውን ለዚህ አገልግሎት በሰጡ ወይም በፈቀዱ ሰዎች ቤት ውስጥ ነበር፡፡ ለምሳሌ የማርቆስ እናት ማርያም በኢየሩሳሌም/የሐ.ሥ.12፡5 -12/፣ አቂላና ጵርስቅላ በሮሜ /ሮሜ16፡3-5/፣ፊልሞና በቈላስይስ /ፊልሞ2፣11፤ቈላ4፡9/፣ ንምፉን በሎዶቅያ/ቈላ4፡15/ ቤታቸውን ለቤተክርስቲያን መሰብሰቢያ እንዲሆን ከፈቀዱት መካከል የሚጠቀሱ /ቅዱሳን/ ሰዎች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በቤታቸው የምትሰበሰበው የምእመናን ኅብረት ቤተክርስቲያን ተባለች እንጂ የአንዳቸውም ቤት «ቤተክርስቲያን» ተብሎ አልተጠራም፡፡

### የቤተክርስቲያን መሠረት

ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ትርጉሙ ምን እንደሆነ ከተመለከትን አሁን ደግሞ ቤተክርስቲያን የተመሠረተችበት መሠረት ምን እንደ ሆነ የሚገልጸውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት እናያለን፡፡ ማንኛውንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ከመሠረቱ ጀምረን ካላወቅን የሚኖረን መረዳት የተሟላ ካለመሆኑም በላይ ጣል በሚገቡ የሰው ሐሳቦች ምክንያት በተሳሳተ መንገድ ልናስብም እንችላለን፡፡ እያንዳንዱ እውነተኛ አማኝ የቤተክርስቲያን አባል እንደመሆኑ መጠን ትክክለኛ ስፍራውን ያውቅ ዘንድ ይህንን ጽኑ የሆነ የቤተክርስቲያን መሠረት አጥበቆ ሊረዳ ይገባዋል፡፡ የሁላችንንም ትኩረት በእጅጉ የሚስበውን ይህንን የቤተክርስቲያን መሠረት የሚያሳውቀን የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ የሚገኘው «ቤተክርስቲያን» የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ተጽፎ በሚገኛበት በማቴ.16፡13-18 ውስጥ ነው፡፡ ይህም ክፍል እንደሚከተለው ይነበባል:-

> «ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሳርያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን:- የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ፤ እነርሱም:- አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ ሌሎችም ኤልያስ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት፡፡ እርሱም:- እናንተስ እኔን ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ? አላቸው፡፡ ስምዖን ጴጥሮስም:- መልሶ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ፡፡ ኢየሱስም መልሶ:- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ፡፡ እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም»፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ እንደተገለጠው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «...በዚህችም አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም...» ብሎ ሲናገር እንሰማዋለን/ቁ.18/፡፡ ጌታችን ይህንን ቃል የተናገረው የ3ቱን ዓመት የማስተማር ዘመኑን እያጠናቀቀ ሳለ ወደ ኢየሩሳሌም ለመጨረሻ ጊዜ ከመውጣቱ በፊት በፊልጶስ ቂሣርያ እያለ እንደነበር የዚህን ንባብ ምዕራፍ ስናጠና እንደርስበታለን/ቁ.21/፡፡ በዚያ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ «ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ» ብሎ በትንቢታዊ ቃል

*(ወደ ገጽ 11 ይዞራል)*

## እውነት አርነት.. ከገጽ 3 የዞረ

ምድራዊ ኑሮአቸውን ለማደራጀት፣ የዋሆችን ለማጭበርበርና የግል ጥቅም ለማጋበስ መንገድ አድርገው ይጠቀሙበታል ማለት ነው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ በዚያ የባርነት ሰፈር ውስጥ አርነት የሚያወጣውን እውነት ያለ አንዳች መሸቃጥ በፍጹም ግልጥነት ይናገሩ ነበር፡፡ እንግዲያስ እነርሱም ራሳቸው ገና በይሉኝታ፣ በፍርሃት፣ በጥቅምና፣ በክብር፣ በዝና...ባርነት ሥር አሉና ፈጽሞ አርነት ሊያወጣ የሚችለውን እውነት ሊያውቁ ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን ሰው ይህንን እውነት እንዴት ያውቃል? ጌታችን ስለዚህ ሲናገር «እናንተ <u>በሴ ብትኖሩ</u> በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ እውነትንም ታውቃላችሁ» ብሏል/ዮሐ.8፡31/፡፡ በእርግጥ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት፣ በመማርና፣ በማንበብ ደረጃ ብዙዎች እውነትን ተረድተው ይሆናል፤ ጌታችን ግን «እውነትን ታውቃችሁ» የሚላቸው በሉ የሚኖሩትን ነው፡፡ በተለያየ የሰው ስትራቴጂ እየተነደፉ በመንፈሳዊ አገልግሎት ስም በእግዚአብሔር ሳይሆን በሰው የተጀመሩ እንቅስቄዎች አማኞችን በተረዱት የእግዚአብሔር እውነት እንዳይኖሩ የሚያደርጉ ናቸው፤ እንዲህ ያሉ እንቅስቄዎችም ምእመናን በዚህ ዘመን የተሳሳተ ሥርዓተ አምልኮ ሳይ ጠመዱ ነጻ ሆነው በእውነተኛ መንገድ እግዚአብሔርን እንዳያመልኩ የሚገፋፉና በማያመኑበትም የሐሰት ትምህርት ተጽዕኖ ሥር እንዲወድቁ የሚያደርጉ የባርነት አገልግሎቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ባለማወቅ በእንዲህ ዓይነት ባርነት የተያዙ

*(ወደ ገጽ 9 ይዞራል)*

## ለጌታ ለአምላክህ ስገድ..ከገጽ 7 የዞረ

ሆነ ከሞተ በኋላ በስግደት እና በጸሎት በመዝሙርም አያመልኩትም ነበር፤ እግዚ አብሔርም የሙሴን መቃብር እንዳይታወቅ ያደረገውስ ለዚህ ሳይሆን ይቀራል? /ዘዳ 34:6፣ ይሁ 9/::

## እውን በምድራችን ቅዱሳን አይመለኩምን?

በእስራኤል ምድር እንኳ አምልኮተ እግዚአብሔር ሳይጀመር በነገደ ኩሽ አማካኝነት በምድራችን የሚታወቅ አምልኮተ እግዚአብሔር እንደነበር በሚተርኩት ሰዎች ዘንድ በዚህችው ምድር ቀደም ባለው ዘመን ዘንዶ ይመለክ እንደነበር የሚነገረው ታሪክ ሲያስከፋቸው ይታያል፤ ታሪክ ደግሞ በዚህ ብቻ አያበም፤ በአርኪዎሎጂ ቁፋሮ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያስረዱት የጨረና የፀሐይ አምልኮ፣ እንደዚሁም «ማሕረም» የተሰኘ ጣዖት እንደነበረ ሲነገርና ሲጻፍ በአፈ ታሪክ ቅዱስ እና ክቡር ሊያደርጉት የፈለጉት ታሪክ ለእነርሱ አእምሮ እየቀለለባቸው ባልሸነፍ ባይነት መከራከራ ቸው አልቀረም፤ አምልኮተ እግዚአብሔር በአሕዛብ አገሮች በማይታወቅበት በዚያን ጊዜ ቀርቶ አሁን እንኳ ብዙ ወገኖቻችን ለዛፍና፣ ለወንዝ፣ ለጠንቋይና ለጨሌ እየሠዉ፣ እየገበሩና እየሰገዱ ምን ያህል በባዕድ አምልኮ ውሰጥ እንዳሉ የሚታየውን የተገለጠ እውነት ማመን የማይፈልጉና ቢቻላቸው ይህንንው የረከሰ አምልኮ የተቀደሰ ታሪክ ሊያበጁለት የሚጥሩ መኖራ ቸው አሳዛኟ ነው፤ እንደዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ብርሃኑን ብርሃን ጨለማውን ጨለማ፣ እውነቱን እውነት ስህተቱን ስህተት፣ ቅዱሱን ቅዱስ ርኩሱን ርኩስ ማለት ያልለመደበት በመሆኑ በምድራችን ላይ ቅዱሳን ተብለው የሚጠሩት ሁሉ በብዙዎች ወገኖቻችን እየተመለኩ የመሆኑን እውነታም ለመካድ አይቸገርም:: «ለቅዱሳንና ለምስሎቻቸው የሚቀርበው ስግደት እና የሚታጠንላቸው እጣን እንዲሁም ወደ እነርሱ የሚጸለየው ጸሎትና ለእነርሱ የሚዘመርላቸው መዝሙርም የእግዚአብሔርን አምልኮ የሚጋራ ሳይሆን ይበልጡኑ እግዚአብሔርን የሚያከብር ነው፤ ምክንያቱም እነዚህ ቅዱሳን የራሱ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ናቸውና፤ ደግሞም ለራሱ ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን ስግደት፣ ጸሎት፣ እና ምስጋና ለእነርሱ አናቀርብም» የሚል መከላከያ በማቅረብ አምልኮተ ቅዱሳንን ምክንያታዊ መንፈሳዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊም ለማድረግ ይጥራል:: ነገር ግን ጥያቄው እውን በምድራችን ቅዱሳን ይመለካሉን? የሚል ብቻ ሳይሆን እውን በምድራችን ቅዱሳን አይመለኩምን? የሚልም ይሆናል፤ በትክክል ለመናገር ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ምስጋናና ክብር ለቅዱሳንና ለተለያዩ ምስሎች ሲቀርብ ይታያል:: አንዳንድ ድርሰቶችም የፈጣሪ ክብር ቅዱሳን እንደሆኑ ለሚታመንባቸው ፍጡራን እንደሚገባቸው በድፍረት ይናገራሉ:: ከነዚህም ድርሰቶች መካከልም አንባቢያን እውነቱን እንዲረዱት ለማስቻል ሲባል ሦስቱን ብቻ ቀጥሎ እናሳያለን::

1. **ለእሉ ክልኤቱ ፍጡራን ስብሐተ ፈጣሪ ይደልዎሙ እስመ ተዐረዩ በክብሮሙ፤**

**<u>ትርጉሙ</u>፡ ለእነዚህ ለሁለቱ ፍጡራን የፈጣሪ ክብር/ስብሐት/ ይገባቸዋል፤ በክብራቸው ተካክለዋልና፤**

ለፈጣሪ የሚገባው ክብር ለሁለቱ ፍጡራን እንደሚገባቸው የሚናገረው ይህ የድፍረት ቃል የሚገኘው «የመስቀል መስተብቍዕ» ተብሎ በሚታወቀው ድርሰት ውስጥ ነው:: ክልዔቱ /ሁለቱ/ ፍጡራን የተባሉትም ማርያምና ዕፀ-መስቀሉ /የመስቀሉ እንጨት/ እንደሆኑ ከዚሁ ድርሰት ውስጥ መረዳት ይቻላል፤ ከፍ ብሎ «ንስግድ ለመስቀል ወለማርያም ድንግል ማለትም ለመስቀል እና ለማርያም እንስገድ» ይላልና:: ታዲያ «ሁለቱ ፍጡራን /ማርያምና ዕፀ መስቀሉ/ የፈጣሪ ክብር ይገባቸዋል» በሚሉት ሰዎች ዘንድ ማርያምና ዕፀ-መስቀሉ አይመለኩም ማለት ይቻላልን?

«ስብሐት» የሚለው የግእዝ ቃል ለአምላክ ብቻ የሚሰጠውን ክብር እንደሚያመለክት የቋንቋው አዋቂዎች ይናገራሉ:: «ለእሉ ክልዔቱ ፍጡራን ስብሐተ ፈጣሪ ይደልዎሙ ማለት የፈጣሪ ክብር ለሁለቱ ፍጡራን ይገባቸዋል» በሚለው ድርሰት ውስጥ ግን «ስብሐት» የሚለው ቃል ለፍጠ -ራን ሲነገር እናያለን፤ ይህም የፈጣሪ ክብር ለፍጡራን እየተሰጠ እንዳለ ያስረዳል፤ ከዚህም በላይ ደግሞ ለሁለቱ ፍጡራን የሚገባቸው ክብር የትኛው ክብር እንደሆነ ድርሰቱ ሲናገር «ስብሐተ ፈጣሪ ማለትም የፈጣሪ ክብር» ብሎ በግልጥ ስላስቀመጠው ነገሩን ለመረዳት ምንም የሚያሻማ አይደለም:: ይህም ድርሰት የሰማይና የምድር ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር ስለራሱ ክብር ሲናገር «እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይህ ነው ክብሬን ለሌላ ምስጋናዬንም ለተቀረፁ ምስሎች አልሰጥም» /ኢሳ.42:8/ ብሎ ከተናገረው መለኮታዊ ቃል ጋር ቀጥተኛ የሆነ ተፃኖ እንዳለው ማንኛውም አንባቢ በቀላሉ ሊረዳው ይችላል::

በመሠረቱ «ማርያም» የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ናት:: በመሆኑም ከማንም በላይ የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐሳብ እንዲሁም የሚያደርገው ነገርና የሚናገረው ቃል ሁሉ የሚገባት ብቻ ሳትሆን የምታከብርም እናት ናት:: ልጇ ኢየሱስ «ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏል» ብሎ የጠቀሰውን ቃል በሚገባ ስለምታውቅ የፈጣሪ

(ወደ ገጽ 10 ይዞራል)

## እውነት አርነት.. ከገጽ 8 የዞረ

ሰዎች በሚረዱት የእውነት ቃል ሊ ኖሩበት ይገባል እንላለን:: እውነትን አውቀናል ማለት የሚችሉትም ያን ጊዜ ነው:: እንዲህ ካደረጉም «በማላምንበት አምልኮና አስተምህሮ በተያዘ ሥርዓት ውስጥ ለምን እኖራለሁ? ሌሎችን አርነት የሚያወጣው የሱ እውነት ነው እንጂ የእኔ ጥበብ ነው እንዴ?» እያሉ በሐ ሳባቸው ሲያሰላስሉት ለነበረው ጥያቄ የሚያሳርፍ መልስን ያገኛሉ፤ እውነት ወደ ሚያጎናጽፋቸው እውነተኛ አርነትም ይወጣሉ !!

- ለእውነት እንጂ በእውነት ላይ ምንም ለማድረግ አንችልምና
  2ቆሮ. 13:8
- በእውነት ላይ አትዋሹ
  ያዕ.3:14
- እውነትም በኢየሱስ እንዳለ በእርሱ ተምራችኋል
  ኤፌ.4:21

## አምላካዊ መልስ.. .. ከገጽ 6

ጊዜ በባሪያው በኤልያስ በኩል እግዚ አብሔር «በኢይዝራኤል ቅጥር አጠገብ ኤልዛቤልን ውሾች ይበሉአታል» ብሎ ተናግሮ ነበር /1ነገሥ.20:23/:: ይህም የእግዚአብሔር ፍርድ «ኢዩ» በአክዓብ ፈንታ በእስራኤል ንጉሥ በሆነ ጊዜ ተፈጽሟል፤ ኢዩ ኤልዛቤልን የገዛ ጃንደረቦቿ በመስኮት እንዲወረውሯት ካደረገ በኋላ ውሾች በሏት፤ ሊቀብሯ ትም በሄዱ ጊዜ ከአናትዋና ከእግርዋ ከመዳፍዋም በቀር ምንም አላገኙም

(ወደ ገጽ 10 ይዞራል)

## ለጌታ ለአምላክህ ስገድ.ከገጽ 12 የዞረ

ክብር በእርሷ ስም ሲቀርብ አሁን በሕይወት ኖራ ብትመለከት ኖሮ እጅግ በጣም ይዘግንናት ነበር፤ ጳውሎስ እና በርናባስ እንዳደረጉትም ልብሷን እስከመቅደድ ደርሳ ታዝን ነበር ለማለት ይቻላል/የሐ.ሥ.14፡13/።

ዕፀ መስቀሉን /የመስቀሉን እንጨት/ በተመለከተም ጌታ የተሰቀለበትና ደሙን ያፈሰሰበት በመሆኑ የፈጣሪ ክብር ይገባዋል የሚለው ኢ-ክርስቲያናዊ አስተሳሰብ በክርስትና ስም ባዕድ አምልኮን ለማስገባት የክርስቲያኖች ጠላት የተጠቀመበት ዘዴ ከመሆን አያልፍም። በአንድ ወቅት እግዚአብሔር አንድ ሥራ የሠራበት ማንኛውም ነገር በቀጣዩ ወቅት እንዲሰገድለትና እንዲታጠንለት የሚያመለከት ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ የለም። ይልቁንስ ሰዎች በራሳቸው መንገድ እንዲህ ቢያደርጉ ባዕድ አምልኮ መሆኑን የሚያሳይ መረጃ ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኛለን። ለምሳሌ ሙሴ በምድረ በዳ የሠራውና የአካዝ ልጅ ንጉሡ ሕዝቅያስ የሰባበረው የናሱ እባብ ታሪክ ይህንኑ ያስረዳል። ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ «በኮረብታ ያሉትን መስገጃዎች አስወገደ፤ ሐውልቶችንም ቀለጣጠመ፤ የማመለኪያ ዐፀዶቹንም ቈረጠ፤ የእስራኤል ልጆች እስከዚህ ዘመን ድረስ ያጥኑለት ነበርና ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ ሰባበረ ስሙንም ነሑሽታን ብሎ ጠራው» የሚል ነው/2ነገሥ.18፡4/፤ በዚህ ንባብ ውስጥ ህዝቅያስ እስራኤል የሚያጥኑለትን ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ እንደሌሎቹ ሀውልቶችና የማምለኪያ ዐፀዶች ተመልክቶና ቆጥሮ በመሰባበሩ አልተወቀሰም ይልቁንስ ከዚሁ ንባብ ቀጥሎ «በእስራኤልም አምላክ በእግዚአብሔር ታመነ ከእርሱም በኋላ ከእርሱም በፊት ከነበሩት ከይሁዳ ነገሥታት ሁሉ እርሱን የሚመስል አልነበረም» የሚል ቃል ስለእርሱ ተጽፎለታል/2ነገሥ.18፡5/፤ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የፈጣሪን ስግደትና መዝሙር እንዲሁም ክብር ለዕፀ መስቀል ማቅረብ የተሰቀለውን ጌታ ከማምለክ ይልቅ የተሰቀለበትን እንጨት ማምለክ እንደሆነ ልናስተጠውለው ይገባል። በመሠረቱ ዕፀ መስቀልና ሌሎቹም ንዋያተ-ቅድሳትም ቢሆኑ እንኳ ከታጠነላቸው፣ ከተሰገደላቸውና ከተዘመረላቸው ከሐውልቶችና ከማምለኪያ ዐፀዶች ተለይተው እንደማይታዩ ሕዝቅያስ ከሰባበረው ከናሱ እባብ ታሪክ ለመረዳት እንችላለን። ስለዚህ በእንዲህ ዓይነት አምልኮ የተያዘች ነፍስ ንስሐ በመግባት ህያው ወደ ሆነው እግዚአብሔር አምልኮ ብቻ ዘወር በማለት አርነት ልትወጣና አርነቷንም ልታውጅ ይገባታል።

2. **ሰላም ለአብ፣ ወለወልድ ሉ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ሰላም ዘአካሎሙ አካሉ ፣ለማርያም ሰላም እንተ ተሳተፈት ስብሐተ እሉ ፤**

**<u>ትርጉሙ፡</u> ለአብ ሰላም ይሁን፤ ለሉ ለወልድም። አካላቸው አካሉ ለሆነ ለመንፈስ ቅዱስም ሰላም ይሁን። የእነርሱን ክብር ለተካፈለች /ለተሳተፈች/ ለማርያም ሰላም ይሁን**» ይላል። */ነግሥ/*

በዚህ ድርሰት ውስጥ በቅድሚያ መንፈስ ቅዱስን በሚመለከት «ዘአካሎሙ አካሉ» የሚለው አባባል የመንፈስ ቅዱስ አካል የአብና የወልድ አካል እንደሆነ የሚናገርና መንፈስ ቅዱስን አካል አልባ የሚያደርግ የአርዮሳውያን አስተሳሰብ እንዳለበት እግረ መንገዳችንን ሳን ጠቁም አናልፍም። በነገረ መለኮት ትምህርት ላይ እንዲህ ያለ ስህተት የሚናገረው ይህ ሰላምታ በተጨማሪ ደግሞ ፍጡር የሆነችውን ማርያምን በፈጣሪ ደረጃ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ስብሐት /ክብር/ የምትሳተፍ እንደሆነች የሚያስቀምጥና በአምልኮተ ሥላሴ ውስጥ አምልኮተ ማርያምን በግልጥ የሚያስገባ ሰላምታ ነው። በአንድ በኩል እኛ እኮ ማርያምን «የጌታ እናት» እንደመሆኗ መጠን እናከብራታለን እንጂ አናመልካትም፤ የፈጣሪ የሆነውንም ክብር ለእርሷ አንሰጥም እየተባለ በሌላ በኩል ደግሞ «ለማርያም ሰላም እንተ ተሳተፈት ስብሐተ እሉ የእነርሱን /የሥላሴን/ ክብር ለተሳተፈች ለማርያም ሰላም ይሁን» የሚባል ከሆነ እንዲህ በሚሉ ሰዎች ዘንድ ማርያም እየተመለከች አይደለምን? ይሁንና ስለ ማርያም ኤልሳቤጥ «በጌታ የተነገረላት ይፈፀማልና ያመነች ብፅዕት ናት» /ሉ.1፡45/ ብላ እንደተናገረችው ትውልድ ሁሉ «ያመነች ብፅዕት ናት» እያለ /ሉ.1፡45፣48/ ከመመስከር ባሻገር በጸሎት በመዝሙርና በውዳሴ ከሥላሴ እኩል ክብርንና አምልኮን ሊያቀርብላት የማይገባ መሆኑን በዚህ ነገር ባለማወቅና የተሳሳቱ ወገኖች ማስተዋል ይገባቸዋል።

3. **ኢንጎስስ እንከ ለከዊነ አግብርተ እግዚአብሔር በፈጺሞ ህገጋት ዐሠርቱ ወስድስቱ... አላ ንትባደር ለከዊነ አግብርተ ማርያም**

**<u>ትርጉም፡</u> አሥራ ስድስቱን ህግጋት በመፈጸም የእግዚአብሔር ባሮች መሆንን አንሻ፤ የማርያም ባሮች ለመሆን እንሽቀዳደም እንጂ ፤**

**/ተአምረማርያም፣ተአምር12ቁ52/**

በተ.ቁ.2. ላይ የተመለከትነው ድርሰት ማርያም ከሥላሴ ክብር እንደምትሳተፍ የሚገልጽ ነበር።

*(ወደ ገጽ 12 ይዞራል)*

## አምላካዊ መልስ.. ከገጽ 9 የዞረ

/2ነገሥ.9፡30-36/፤ እግዚአብሔር በኤልያስ የተናገረው የፍርድ ቃል በተግባር ተፈጸመ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን ቀጥተኛ የወንጌል እውነት እንዳያምኑና እንዳይኖሩበት አቅጣጫ በማሳት የክርስቲያን ካባ ለብሶ ክፋትን የሚያገለግለውን የኤልዛቤልን መንፈስ እግዚአብሔር በፍርድ የሚበቀልበት ጊዜ ይመጣል፤ እግዚአብሔር በኤልዛቤል ብቻ ላይ ሳይሆን ከእርስዋ ጋር አብረው በእግዚአብሔር ላይ ባመፁት ሁሉ ላይ ይፈርዳል። ጌታ ኢየሱስ ለትያጥሮን ቤተክርስቲያን ይህንን የፍርድ ቃል ሲናገር «...ንስሐ እንድትገባ ጊዜ ሰጠኋት ከዝሙትዋ ንስሐ እንድትገባ አልወደደችም። እነሆ በአልጋ ላይ እጥላታለሁ ከእርስዋ ጋር የሚያመነዝሩትንም ከሥራዋ ንስሐ ባይገቡ በታላቅ መከራ እጥላቸዋለሁ ልጆችዋንም በሞት እገድላቸዋለሁ» ብሏል/ራእ.2፡21-23/።

### ስለዚህ ንስሐ ግቡ

በኤልዛቤል አሠራር ዙሪያ ያላችሁ ወገኖች ሆይ ይህን የከበረውን የእግዚአብሔርን ልጅ ቃል ስሙ። ከሚመጣውም አስፈሪ የእግዚአብሔር ፍርድ ትድኑ ዘንድ ዛሬ ነገ ሳትሉ አሁኑኑ ንስሐ ግቡ። ጌታ ኢየሱስንም እመኑትና ተከተሉት፤ እርግጥ ኤልዛቤል በብዙ ብልሃት እናንተን ለማታለል ትሞክራለች፤ ነገር ግን ንቁባትና ከልብ ታምኑበት ዘንድ ከእርስዋ ተለይታችሁ በንስሐ ወደ ኢየሱስ ኑ። «ከእርስዋ ጋር የሚያመነዝሩትን ከሥራዋ ንስሐ ባይገቡ በታላቅ መከራ እጥላቸዋለሁ ልጆችዋንም በሞት እገድላቸዋለሁ» ብሎ ጌታችን የተናገረው ሁሉ ሳይደርስባችሁ ለንስሐ ፍጠኑ /ራእ2፡22-23/፤ ያለማወቃችሁም ወራት አሁኑኑ ያብ፡፡ በነፍሳችሁም ትድናላችሁ

**«እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤ ቀን**

**ለአስተያየቶቻችሁና ለጥያቄዎቻችሁ**

**14787**

## ቤተክርስቲያን.. ..

ከገጽ 8 የዞረ

መናገሩ በጊዜው ገና ቤተክርስቲያን ተሠርታ እንዳልነበረ ያመለክተናል፡፡ በእርግጥም በደሙ በሚደረግ ቤዛነት ሕዝብን ከነገድ ከቋንቋ ሳይዋጅ ቤተክርስቲያን ልትሠራ እንዴት ትችላላች? ቤተክርስቲያንን በገዛ ደሙ እንደዋጃት የሚያስረዳ ግልጽ ንባብ እናገኛለንና/የሐ.ሥ.20፡28/፡፡ ስለዚህ በክርስቶስ ሞት የኃጢአት ዕዳ ከመከፈሉ በፊት ቤተክርስቲያን እንዳልተሠራች ልንገነዘብ እንችላለን፡፡

አሁን ደግሞ «...በዚህችም አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም...» ብሎ ጌታችን በተናገረው ቃል ውስጥ ያሉትን ሁለት ዋና ዋና ኃይለ ቃላትን እንመልከት፡፡

### 1. በዚህችም ዓለት ላይ

ጌታ ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን የሚሠራበትን መሠረት ሲገልጥ «በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያንን እሠራለሁ» ብሏል፡፡ ከዚህም ቃል የቤተክርስቲያን መሠረት «ዓለት» እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በማቴ7፡24-27 የተመዘገበውን የጌታችንን ምሳሌ ስናነብ ልባም ሰው ቤቱን በዓለት ላይ እንደሚሠራና ያንንም በዓለት ላይ የተመሠረተ ቤት ዝናብ ቢወርድም ጐርፍ ቢመጣም ነፋስ ቢነፍስም ፈጽሞ ሊወድቅ እንደማይችል ያስረዳል፡፡ በተራ ኒው ግን ሰነፍ ሰው የሚሠራው በአሸዋ ላይ የተመሠረተ ቤት ዝናብ ሲወርድ ጐርፍ ሲመጣ ነፋስም ሲነፍስ ታላቅ አወዳደቅ እንደሚወድቅ ይገልጻል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ኢየሱስ ክርስቶስ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ «ልባም ሰው» ነው፡፡

«በዚህችም ዓለት ላይ...» የሚለውን ይህንን ቃል የሚያነቡ ሁሉ «ይህች ዓለት ምንድር ናት?» ብለው መጠየቻው የማይቀር ነው፡፡ ጌታችን ከዚህ ንባብ ቀደም ብሎ «አንተ ጴጥሮስ ነህ» ካለ በኋላ «በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ» ብሎ መናገሩን በመመልከት በዚህ ንባብ ውስጥ ዓለት የተባለችው «ጴጥሮስ ነው» የሚል የተሳሳተ መረዳት መኖሩ ይታወቃል፡፡ ይህም መረዳት ንባቡ የቀረበበትን ሰዋስው በተለይም የሴን ጾታ ማስተዋል ካልቻለ አእምሮ የሚወጣ ነው፡፡ ጌታችን «አንተ ጴጥሮስ ነህ» የሚለውን ቃል የተናገረው በተባዕታይ ጾታ እንደሆነ ያስተዋለ አንባቢ «በዚ ህችም ዓለት» ላይ ብሎ ዓለት የሚለውን ቃል ወደ እንስታይ ጾታ ሲለውጠው **ዓለቷ ጴጥሮስ ነው** ማለት አይችልም፤ ይህ የተባዕታይንና የእንስታይን ጾታ ማደባለቅ ነው፡፡ በዚህ ፈንታ ግን ጌታችን «በዚህች» በሚለው ጠቋሚ ቃል በእንስታይ ጾታ የጠራት ዓለት ምንድናት? ብሎ በመጠየቅ ምላሹን ከዚሁ ንባብ ውስጥ ያፈላልጋል፡፡ በሰው ሐሳብ ሳይጠላለፍ በመንፈስ ቅዱስ በተኘ ኀሊና ሆኖ እስካነበበ ድረስም ምላሹን በዚሁ አንቀጽ ውስጥ በቅርቡ ያገኛል፡፡ «በዚህች» በሚለው የቅርብ አመልካች ቃል የተጠቆመችው የዚህች ዓለት ምንነት ኢየሱስ ሴን በሚናገርበት በዚያው ሰዓት የተገለጠ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህም አንባቢ ው ዓይኖቹን ከፍ አድርጐ ወደ ቁጥር 16 ቢመለከት ጌታችን ስለማንነቱ ለደቀመዛሙርቱ ላቀረበው ጥያቄ ጴጥሮስ የመለሰውን አጭርና ግልጽ መልስ ያገኛል፡፡ እርሱም «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» ብሎ በሥጋና በደም ሳይሆን በሰማያዊ መገለጥ የተናገራት ቃል ናት፡፡

በግሪክ ቋንቋ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ጴጥሮስ የሚለው ቃል «πετρος /ፔትሮስ/» ተብሎ የተጻፈ ሲሆን ዓለት የሚለው ቃል ግን «πετρα /ፔትራ/» ተብሎ ተጽፏል፤ ይህም በሁለቱ ቃላት መካከል ግልጽ የሆነ የትርጉም ልዩነት እንዳለ ያሳያል፤ «ፔትሮስ» ማለት ከዓለት የተከፈለ ድንጋይ /ጡብ/ ማለት ሲሆን «ፔትራ» ማለት ራሱ ሙሉው ዓለት ነው፡፡ ጌታችንም ቤተክርስቲያኔን በፔትራ /በንጥፍ ዓለት/ ላይ እመሠርታለሁ አለ እንጂ በፔትሮስ /በጡብ/ ላይ እመሠርታለሁ አላለም፤ ስለሆነም የቤተክርስቲያን መሠረት «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ» የምትለው የእምነት ቃል ናት እንጂ ጴጥሮስ አለመሆኑን አንባቢው ሊያስተውል ይገባል፡፡ ይህችም የእምነት ቃል ስለክርስቶስ የምትናገር ስለሆነ የቤተክርስቲያን መሠረት ራሱ ክርስቶስ ነው ቢባል ትክክል ነው/1ቆሮ.3፡11/፡፡

> **ይህን ቃ የሕይወት መመሪያ ያደረገ ክርስቲያን እኔ የምሰበሰብበት መንፈሳዊ ጉባዔ የተመሠረተው በምን ላይ ነው? ብሎ በማስተዋል ሊመረምር ይገባዋል፡፡**

ይህንን ቃል የሕይወት መመሪያ ያደረገ ክርስቲያን እኔ የምሰበሰብበት መንፈሳዊ ጉባዔ የተመሠረተው በምን ላይ ነው? ብሎ በማስተዋል ሊመረምር ይገባዋል፡፡ በዘመናችን በየስፍራው የሚቋቋሙት ድርጅታዊ ገጽታ ያላቸው አብያተክርስቲያናት የቆሙበትን መሠረት በጥንቃ ልንመረምር ያስፈልጋል፡፡ ለቤተክርስቲያን ህልውና መሠረት የሆነውን «ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነው» የሚለውን የእምነት ቃል ወደ ጐን በመተው ወይም ትኩረት በመንፈግ መሠረት ተደርገው ያልተነገሩትን ሌሎች መንፈሳውያን ትምህርቶችና ሥርዓቶች መሠረት ማድረግ አሳዛኙ የክርስቲያኖች ውድቀት እየሆነ መጥቷል፤ ከ4ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የሚታየውን የዓለማዊቷን ቤተክርስቲያን መለየት ስንመለከት ዋነኛ ምክንያቱ ሥልጣንን፣ ጥቅምን፣ ክብርንና ማዕርግን ማስጠበቅ ቢሆንም ማሳበቢያ የሆኑት መንፈሳዊ ምክንያቶች ግን፣ ክርስቶስ አንድ ባሕርይ ወይስ ሁለት ባሕርይ ነው? ማርያም ታድናለች ወይስ አታድንም?፣ ጥምቀተ ህፃናት ልክ ነው ወይስ አይደለም? ሥዕል ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም? በጌታ እራት ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ ወደ ሥጋና ደም ይለወጣል ወይስ አይለወጥም? የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሲገለጡ እንዴት ነው? በልሳን መናገርና አ ጠቃሙን የምንረዳው እንዴት ነው? የቤተክርስቲያን አስተዳደር በሽማግሌዎች ወይስ በካህናት ይሁን? የሚሉትና የመሣሠሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ «ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው» የሚለውን የቤተክርስቲያን መሠረት የማይተኩና አንዳንዶቹ ደግሞ ፈጽሞውኑ ከእውነት የራቁ ናቸው፡፡ በእነዚህ አርእስተ ጉዳዮች ያሉት እውነተኛ ትምህርቶችም ቢሆኑ ለቤተክርስቲያን እንደ ዋና መሠረት ታይተው ጉባዔ የሚመሠረትባቸው ቤተክርስቲያን የሚከፈልባቸው አዲስ ስም የሚወጣባቸው ምክንያቶች መሆናቸው አሳዛኝ ነው፡፡ ይሁንና ከዚህ አስተሳሰብ ተለይተው መሠረታቸውን በጥልቀት የተመለከቱ በሁሉም ስፍራ የሚገኙት የእውነተኛ ክርስትና ቀሬታዎች ግን ራሳቸውን «ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነው» በሚለው መሠረት ላይ ያገኙታል!!

በየስፍራው እየተዘዋወሩ ሕዝብን ሰብስበው አዳዲስ የክርስቲያን ጉባኤያትን ወይም አጥቢያ ቤተክርስቲያናትን የሚመሠርቱ የወንጌል አገልጋዮች ለዚያ ጉባዔ የሚጥሉትን መሠረት ምን እንደኾነ ለይተው ሊያውቁ ይገባቸዋል፡፡ ማንኛውም አገልጋይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባላስቀመጠው መሠረት ላይ እንዳይመሠርት በፈሪሃ እግዚ አብሔር ሆኖ ሊጠነቀቅ ይገባዋል፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም ይህንኑ አጥብቆ ሲያስረዳ «ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊ መሠርት አይችልምና፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» ይላል /1ቆሮ3፡11/፡፡ በዚህ ንባብ ውስጥ

*(ወደ ገጽ 13 ይዞራል)*

## ለጌታ ለአምላክህ ስገድ..ከገጽ10 የዞረ

ይህ ደግሞ ከዚህ በባሰ ደረጃ ሰዎች ለእግዚአብሔር ባሮች ለመሆን መሻት እንደሌለባቸው በምትኩ ግን ለማርያም ባሮች ለመሆን እንዲሽቀዳደሙ የሚናገር ሌላው ክህደት ነው፤ ይህ ክፍል ሲነበብላቸው ምንም ሳያስተውሉ በየዋህነት ብቻ ከንፈራቸውን እየመጠጡ፣ እጃቸውን እያርገበገቡ አሜን አሜን የሚሉ ምእመናን ምንኛ ያሳዝናሉ! በጌታችን እናት በቅድስት ማርያም ስም እየተሰበከ ያለው ይህ አምልኮ ባዕድ አምልኮ መሆኑ እንዳይነበት ሰይጣን የብዙዎችን ማስተዋል የጋረደበት ዘመን ላይ እንገኛለን፤ በመሠረቱ ተአምረ ማርያም በግእዝ ብቻ ሳይሆን ባማርኛም ተተርጉሞ ስለሚገኛ ማንም ምእመን ሊያነበው የሚችል በመሆኑ ይህ አባባል ማርያም እንድትመለክ የሚያደርግ ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም:: ደራሲው ተሳስቷል ወይም ክዷል ላለማለት ብቻ «የእመቤታችንን ፍቅር ከመጠን በላይ ለመግለጥ እንጂ ለእግዚአብሔር ባሮች መሆንን ትታችሁ ለማርያም ባሮች ሁኑ ለማለት አይደለም» የሚለው ከንቱ ክርክር ውሸቱን ውሸት ለማለት ከመፍራት አልያም ስህተትን ጨርሶ ላለመቀበል ከመፈለግ የሚመጣ በግልጽ የሚያስታውቅ አልሸነፍ ባይነት ነው:: በመሆኑም በዚህ ሁሉ የሚያባብል ቃል እየተደለሉ ይህን የክህደት ቃል ትተው ወደ እግዚአብሔር ተገዢነት ብቻ ዘወር ለማለት ያልቻሉ የዋሃን እናቶችና አባቶች እንዲሁም ወጣት ወንድሞችና እኅቶች «እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተወሙ ከእናንተም ይሸሻል ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባችኋል» ለሚለው ቃል እጃቸውን በመስጠት ሊማረኩ ይገባቸዋል /ያዕ.4፡7-8/::

ረዘም ላለ ጊዜ ግልጽ በሆነና ስውር በሆነ የባዕድ አምልኮ ባርነት ውስጥ እያወቁም ይሁን ባለማወቅ ተይዘው የኖሩ ሰዎች የእውነት ወንጌል በርቶላቸው የእውነተኛውና የብቸኛውን አምላክ ማንነት ባወቁ ጊዜ እስከዚያን ጊዜ ማስተዋላቸውን የጋረደውንና በተለያዩ መንፈሳዊ እና ባህላዊ በሆኑና በሚመስሉ አስተሳሰቦች ያታለላቸውን የነፍሳቸውን ጠላት «ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏል» በማለት ሊወሙት ይገባል:: በዚህ መልክ በእምነት ቢወሙት ወዲያውኑ ከእነርሱ ይሸሻል:: እነርሱም ሕያው ለሆነው ለአንድ አምላክ ብቻ በምስጋናና በውዳሴ፣ በመዝሙርና በጸሎት ለሱም በመገዛት በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ እግዚአብሔርን ብቻ እያመለኩ ሊኖሩ ይገባቸዋል::

**ያድን ዘንድ ወድማይችል አምላክ የሚጸልዩ እውቀት የላቸውም**
ኢሳ.45፡20

—//—

## የምታገለግሉት ጌታ.. ከገጽ 3 የዞረ

መልካም ሐሳብ ሁሉ የእግዚአብሔር ሀሳብ አይደለም ወደሚል መደምደሚያ ያደርሰናል፤ ስለሆነም ማናቸውም በጎ ነው የሚባል የወንጌል አገልግሎት ሁሉ ከሁሉ በፊት እንደ እግዚአብሔር ፈድ መሆኑ ሊረጋገጥለት ይገባል::

ወንጌልን በምናገለግልበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ፈድ ውጪ እንድናገለግል የሚያደርጉን በርካታ ምክንያቶች አሉ፤ ከእነዚህም መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

1. <u>ሰውን ደስ ለማሰኘት ማገልገል፤</u>
በአገልግሎታችን ውስጥ የሰውን ፈድ ለመፈጸም ወይም ሰውን ደስ ለማሰኘት ብንፈልግ ውጤቱ ከእግዚአብሔር ፈድ መውጣት ይሆናል፤ ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር «ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኛ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኛ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም» ይላል /ገላ1፡10/:: «አድማጮቼ ምን ብነግራቸው ምንስ ብሰብክላቸው ደስ ይሰኛሉ» ብሎ የሚያገለግል አገልጋይ እርሱ ለእግዚአብሔር ወንጌል አደራ አልታመነም፤ በመሆኑም የወንጌል አገልግሎትን አደራ የተቀበለ አገልጋይ ሰውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ብቻ በመናገርና በመኖር በታማኝነት ሊያገለግል ይገባዋል:: ጳውሎስ ስለዚህ ዳግመኛ ሲናገር «ወንጌልን አደራ ይሰጠን ዘንድ በእግዚአብሔር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን እንዲሁ እንናገራለን፤ ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ደስ እንደምናሰኛ አይደለም፤ እንደምታውቁ እያቆላመጥን ከቶ አልተናገርንም» ይላል/1ተሰ2፡4-5/::

2. <u>ራስን ማስቀደም፡</u>
አገልጋይ የራሱን ጥቅም ከመፈለግና የራሱን ዝነኛነት ከመሻት ፈጽሞ ካልወጣ በሚያገለግለው አገልግሎት ላይ የግል ፈዱ ጣል እየገባበት ከእግዚአብሔር ፈድ ያወጣዋል:: ራሱን ካልካደና የራሱንም ጥቅም ወደ ጎን ካልተወ ሌሎችን መጥቀም አይችልም፤ በአንድ በኩል የራሱን ጥቅምና መብት ለማስጠበቅ የሚጥር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሌላውን መጥቀም የሚሻ አገልጋይ ለጌታ አይሆንም፤ የራሱ ጥቅም የሚመራው ሰው ለጌታ አይገዛም፤ እውነትንም ይጥላል፤ እንደዚህ ያሉ ሰዎች ስለጥቅማቸው ሲሉ እውነትን ያጣምማሉ፤ ጲላጦስ በደል እንደሌለበት እየመሰከረ ጌታን የገረፈውና ይሰቀል ዘንድ አሳልፎ የሰጠው «ይህንስ ብትፈታው የቄሣር ወዳጅ አይደለህም» /ዮሐ.19፡12/ ባሉት ጊዜ እንደሆነ ግልጥ ነው:: ኢየሱስን አሳልፎ ባይሰጣቸው የሚደርስበት ችግር ሊኖር እንደሚችል አስቧልና ለሚያውቀው እውነት ከመገዛት ይልቅ «የሕዝቡን ፈድ ሊያደርግ ወድዶ በርባንን ፈታላቸው፤ ኢየሱስንም ገርፎ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጠው» /ማር15፡15/:: በኋላም በጲላጦስ መንገድ የሄዱ ስለ ሆዳቸው ሲሉ ማሰናከያን ስላደረጉት ሰዎች ሐዋርያው ሲናገር «እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና» ይላል /ሮሜ.16፡17/:: ሥጋዊ ጥቅማቸው፣ ምድራዊ ሥልጣናቸው እንዳይነካ ሲሉ አሁንም ኢየሱስን አሳልፈው የሚሰጡ ላመኑት እውነት ከመታዘዝ የወጡ አገልጋይ ነን የሚሉ በሁሉም ሥፍራ የሚታጡ አይደሉም፤ የምናገለግለውን ሕዝብ በተሰጠን ጸጋ ልንጠቅም እንጂ እንደ ርስትና ጉልት ልንጠቀምበት አልተላክንም፤ ስለሆነም ጳውሎስ «የክርስቶስ ሐዋርያት እንደመሆናችን ልንከብድባችሁ ስንችል ከእናንተ ቢሆን ወይም ከሌሎች ክብርን ከሰው አልፈለግንም:: ነገር ግን ሞግዚት የራስዋን ልጆች እንደምትንከባከብ፣ በመካከላችሁ የዋሆች ሆነን እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃችን ነበር» ይላል/1ተሰ.2፡6-8/:: በሌላም ስፍራ «በአንድ ስንኳ እንዳንከብድ ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም» ይላል /2ተሰ.3፡8/:: ይህ ሁሉ ስለመብል ወይም ስለሹመት፣ ወይም ስለደሞዝ ሲሉ ሰውን ደስ ወደማሰኘት ለሄዱትና ከእውነተኛ አገልጋይነት ለወጡት ወደ ትክክለኛ የአገልግሎት መስመር የሚመልስ መልእክትና ማስጠንቀቂያ ነው:: በሰዎች ዘንድ

*(ወደ ገጽ 16 ይዞራል)*

## ቤተክርስቲያን.. ከገጽ 11 የዞረ

የተመሠረተው መሠረት «ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» ሲባል ጌታችን «ዓለት» ብሎ ከገለጠው የጴጥሮስ ምስክርነት ጋርም የሚስማማ ነው፤ «ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነው» የሚለው ቃ ኢየሱስ ክርስቶስን በማንነቱ ይገልጠዋልና:: ይህም እውነት የገባቸው አገልጋዮች ኢየሱስ ክርስቶስ በመሠረተው መሠረት ላይ ያንፃሉ እንጂ ሌላ መሠረት አይጥሉም፤ ከዚህ ያነሰ መሠረት ግን ዓለት ሊሆን አይችልም::

## 2. የገሃነም ደጆች አይችሏትም

ልባም ሰው የሠራውንና በጽኑ ዓለት ላይ የተመሠረተን ቤት ዝናብ ወርዶ ጐርፍ ጐርፎ፣ ነፋስ ነፍሶ ቢ ገፋውም ሊወድቅ እንደማይችል የተረጋገጠ ነው/ማቴ7:24-25/:: ዝናብ፣ ጐርፍና ነፋስ በክርስቲያኖች ላይ ስለ ወንጌል የሚደርስ ነቀፋን፣ ስደትንና የተለያየ መከራን እንዲሁም የስህተት ትምህርትን ሊያመለክቱ ይችላሉ:: እነዚህም በጽኑ መሠረት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተመሠረተችውን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ቢገፏትም ሊጥሏት አይችሉም:: ቤተክርስቲያንን በተመለከተ «የገሃነም ደጆች አይችሏትም» የሚል ጽኑ ቃ ከቤተክርስቲያን መሥራች ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ስንሰማ ልባችን በድል ስሜት ይሞላል:: ለመሆኑ የገሃነም ደጆች ምንድር ናቸው?

«የገሃነም ደጆችም አይችሏትም» በሚለው ባማርኛው ንባብ ውስጥ «ገሃነም» የሚለው ቃ በሌሎች ቋንቋዎች «ሲኦል» ተብሎ የተተረጐመ ቃ ነው:: ለምሣሌ በግእዙ አዲስ ኪዳን ውስጥ «ወአናቅጸ <u>ሲኦል</u> ኢይኄይልዋ ማለትም የሲኦል ደጆችም አይችሏትም» ተብሏል:: በግሪኩ πυλαι <u>αδου</u> ου κατισχυσουσιν αυτης ሲባል በእንግሊዝኛውም «the gates of <u>hell</u> shall not prevail against it» ይላል፤ በመሠረቱ <u>αδου</u> የሚለው ግሪክና <u>hell</u> የሚለው የእንግሊዝኛ ቃ «ሺኦል» ለሚለው የዕብራይስጥ ቃ ፍቺ ሆነው ያገለገሉ ቃት ሲሆኑ ግእዙም ሉን እንዳለ በመውሰድ ሲኦል ብሎታል:: «ሲኦል» የሚለው ቃ ከሞት ጋር የተያያዘ ትርጉም እንዳለው ግልጽ ነው/1ቆሮ15:55/፤ ሲኦል ኃጢአተኛ የሞት ፍርድን የሚቀበልበት የሥይ ስፍራ ነው/ሉ16:23/:: ስለዚህ ዋነኞቹ የሲኦል ደጆች ሞትና መውጊያው ናቸው ቢባል ትክክል ነው:: የሞትም መውጊያ ኃጢአት እንደሆነ ተጽፏል /1ቆሮ15:56/:: ቤተክርስቲያንን ግን እነዚህ የገሃነም ደጆች የሆኑት ሞትና ኃ ጢአት እንደማይችሏት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አረጋግጦ ተናገረ:: የዚህም ምክንያቱም ቤተክርስቲያን የተመሠረተችበት ዓለት ማለትም «ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነው» የሚለው እውነት ጽኑዕ ስለሆነ ነው፤ ይልቁንም ኢየሱስን <u>የሕያው</u> እግዚአብሔር ልጅ ነው ብለው የሚያምኑ ክርስቲያኖች ሞትና መውጊያውን ሊፈሩት አይችሉም፤ ኢየሱስ <u>የሕያው</u> እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በመስቀል ላይ በሞተ በ3ኛው ቀን ከሞት በመነሣት በተግባር አረጋግጧልና/ሮሜ1:4/፤ መላእክትም «<u>ሕያውን</u> ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጉታላችሁ?» ብለው በማለዳ ወደ ኢየሱስ መቃብር መጥተው ለነበሩ ሴቶች ተናግረዋል/ሉ24:5/፤ ሴቶቹም «<u>ሕያው ነው</u> የሚሉ የመላእክትን ራእይ አየን» እያሉ መስክረዋል /ሉ24:23/፤ ጌታችንም በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ <u>ሕያው</u> ሆኖ ለደቀመዛሙርቱ ራሱን አሳይቷቸዋል/የሐ.ሥ1:3/:: ጴጥሮስም በመልእክቱ ውስጥ ሲጽፍ «በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን <u>ሕያው ሆነ</u>» በማለት ይናገራል/1ጴጥ3:18/:: ኢየሱስ የሕይወት ምንጭ የሆነውና ዘላላማዊ ሕይወት ያለው የአብ ልጅ በመሆኑ በዚህ በሕይወት ኃይል ከሙታን ተነሥቷል:: ያ በአብ ያለው ሕይወት በእርሱም ነበር /ዮሐ1:4/፤ ይህም ሕይወት መለኮታዊ ህይወት ነው፤ ስለዚህ ፍጻሜ የሌለው ህይወት ብቻ ሳይሆን ጅማሬም የሌለው ሕይወት ነው:: በአባቱ ያለው ያ ሕይወት የእርሱም ሕይወት የሆነለት ይህ ልጅ /ኢየሱስ/ ለእኛም የሰ ጠን ሕይወት ያንኑ በአብ ዘንድ ያለውን መለኮታዊ ሕይወት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ሲያስረዳ «ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን ከአብ ዘንድ የነበረውን ለእኛም የተገለጠ ውን የዘላለምን ሕይወት እናወራ ላችኋለን» ይላል /1ዮሐ.1:2/:: የእግዚአብሔር ቃ እንደሚነግረንም ሰዎች እርሱን ባመኑ ጊዜ ኢየሱስ ራሱ ወደ እነርሱ ይገባል/ራእ3:20/፤ ኢየሱስ ወደ ልባቸውና ወደ ኑሮአቸው የገባ አማኞችም የመለኮታዊ ሕይወት ባለቤት ይሆናሉ፤ በሌላ አነጋገር የሚያገኙት የዘላለም ሕይወት ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ማለት ነው፤ «እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው» ተብሎ እንደተጻፈ /1ዮሐ5:20/::

የሞትና የሲኦል መክፈቻ እንዳለው ገልጦ የነገረን ክርስቶስ /ራእ1:18/ «የገሃነም/የሲኦል/ ደጆች አይችሏትም» እያለ ቤተክርስቲያንን በተመለከተ የተናገረው ይህ እርግጠኛ ቃ የሞት አበጋዝ የሆነው ዲያብሎስ በዙሪያችን ለሚያሰማን የመከራና የሞት ድምፅ ጆሮ እንዳንሰጠው ያደርገናል:: የክርስቶስ ኢየሱስ በመሆናችን ክርስቶስን ከበር ውጪ አውጥታ የሰቀለችውና ታሪኩንም በሞትና መቃብር ለመደምደም ሙከራ አድርጋ የነበረችው ዓለም ብትጠላንም ሆነ ብታሳድደን እስከሞት ድረስ ታማኞች እንድንሆን የሚያጠነክር አስተማማኝ ዋስትና ከኢየሱስ አግኝተናል:: ድንጉጥና ፈሪ የሆነው ልባችን ከዓለም የሚደርስብንን ነቀፋ ገና ሲሰማ በሞት ፍርሃት ቢታሠርም «የገሃነም ደጆች አይችሏትም» የሚለውን ድምፅ ባስታወሰ ጊዜ የሞት ፍርሃቱ ሁሉ ከላዩ ይገፈፋል:: መጽሐፍ ቅዱሳችን ኢየሱስ ሰው የመሆኑ ዓላማ ይህ መሆኑን ሲገልጥ «እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ ነው በሕይወታቸውም ሁሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ» ይላል /ዕብ2:14/::

ስለሆነም ሰይጣን እኛን ሊያስፈራራበት የሚችለው ትልቁ መሣሪያው ሞትና መውጊያው በኢየሱስ የተሰበረ መሆኑን ከልብ በማመን ከሞት ፍርሃት ነጻ ልንሆን ያስፈልጋል:: በእርግጥ መሠረቷ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ በሆነላት አንዲቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ አባል እንደሆኑ እርግጠኛ የሆኑ ምእመናን «በዚህችም አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም» በሚለው የጌታችን የማረጋገጫ ቃ ስለሚያምኑ በዘመናቸው ሁሉ በሞት ፍርሃት ሊታሠሩ አይችሉም:: ሞት ይይዘው ዘንድ ያልቻለው /የሐ.ሥ.2:24/:: የሕያው እግዚአብሔር ልጅ በደሙ የዋጃትና ራስ የሆነላት ይቺ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን የሲኦል ደጆች የሆኑት ሞትና መውጊያው እንዴት አድርገው ሊያናውጧት ይችላሉ? በእርግጥ ፈጽሞ አይችሉም::

ስለዚህ ዛሬ ቤተክርስቲያን ልቧን አስፍታ ድምጿን ከፍ አድርጋ:-

«ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ፤ ሲኦል ሆይ ድል መንሣትህ የታለ፤ የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው፤ የኃጢአት ኃይል ሕግ ነው፤ ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን» /1ቆሮ.15:55-57/

ብላ መዘመር ትችላለች::

—//—

እስስት በምሳሌ አፉየ
ወእነግር ዘኅቡእ
ዘምእምትካት
ማቴ13፡35

# ህሪስት ጥበብ



በምሳሌ አፌን እከፍታለሁ
አለም ከተፈጠረ ጀምሮ
የተሰወረውን እናገራለሁ።

## ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰ ጠ/ኤፌ.5፡26/

ከ2500 ዓመታት በፊት የነበረው አርጤክሲስ የተባለው የፔርሺያ ንጉሥ በዘመኑ ከጎረቤት አገር ጋር ጦርነት አጋጠመውና በጦርነቱ ድል አደረገ። የተጋጣሚውንም አገር ገዢ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር ማረከው፤ ከዚያም አርጤክስስ የማረከውን አገረ -ገዢ በፊቱ አቅርቦ ያለውን ንብረት ሁሉ ጠየቀው፤ አገረ ገዢውም ሁሉንም ዘርዝሮ ተናገረ። አርጤክሲስም «እነዚህን ልጆችህ ለእኔ ምርኮኞች ሆነዋል፣ እኔ እንደባሪያ ልሸጣቸው እችላላሁ፣ ልጆችህ ነጻ እንዲወጡ ምን ትሰጠኛለህ?» አለው፤ ገዢውም «ያለኝን ሁሉ እሰጥሃለሁ» አለው። አርጤክሲስም መልሶ በጣም ጥሩ! ልጆችህ በነጻ ሊሄዱ ይችላሉ፤ አሁን ለአንተ ያለው ነገር ሁሉ የእኔ ነው» አለው፤ በመቀጠልም «ሚስትህም እዚህ አለች፣ እርሷም የእኔ ምርኮኛ ናት እንደባሪያ ልሸጣት እችላለሁ፤ ለሚስትህስ ነጻነት ምን ልትሰጠኝ ትችላለህ?» አለው፤ ገዢውም እንደገና «ያለኝን ሁሉ» ሲል መለሰ። አርጤክሲስ ግን «አይደለም ይህን ማድረግ አትችልም፤ አንተ ያለህን ነገር ሁሉ ልጆችህ ነጻ እንዲወጡ ስለሰጠኸኝ አሁን የእኔ ሆኗል፤ ምንም የቀረህ ነገር የለም» አለው፤ አገረ ገዢውም መልሶ «እኔ ስለ እርስዋ የራሴን ሕይወት አሳልፌ እሰጣለሁ፤ የእኔን ሕይወት ውሰድ፣ እርስዋም በነጻ ትሂድ» አለው። ከዚህ በኋላ አርጤክሲስ ተገርሞ «ሁሉም ቤተሰብ ያለምንም ክፍያ በነጻ ይሂድ ብሎ ለቀቃቸው። እነርሱም ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላ፣ ባልንጀሮቻቸውን አግኝተው ስለአርጤክሲስ ያዩትና የሰሙትን ሁሉ መነጋገር ጀመሩ ብርታቱን፣ ብልጥግናውን፣ ክብሩን፣ በተለይ ግን ለገዢውና ለቤተሰቡ ያደረጋቸውን የምሕረት ሥራዎች ይነጋገሩ ነበር፤ ይህ ሁሉ ሲነገር የአገረ ገዢው ሚስት ግን ጸጥ ብላ ነበር። በመጨረሻም አገረ ገዢው «ስለእርሱ ምንም የተለየ ነገር አታስታውሺምን?» ሲል ሚስቱን ጠየቃት፤ እርሷም «ምንም የለም» አለች። በጣም ተገርሞ «ለእኛ ጥሩ ስለነበረው ስለዚህ ሰው የምትዪው ነገር ምንም ልታስቢ እንዴት አልቻልሽም?» አለ። እርስዋም መልሳ «እኔ ባሪያ እንዳልሆን ሲል የራሱን ሕይወት ስለ እኔ አሳልፎ ለመስጠት ካዘጋጀው ሰው በቀር ስለሌላ ሰው ላስብ እንዴት እችላለሁ? ስለ ሌላ ስለማንም ላስብ አልችልም» አለችው።

ቤተክርስቲያንም ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ እስከመስጠት ድረስ ከወደዳት ከእርሱ ከኢየሱስ በቀር በሌላ በማንም ሐሳብ ልትያዝ አይገባትም !!

## ስለ ክርስቶስ ምን ትላላችሁ?

- ፈሪሳውያን፦ ስለ ኢየሱስ ምን ትላላችሁ?
  «ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ይበላል» /ሉ፲5፡2/
- ቀያፋ፦ አንተስ ስለ እርሱ ምን ትላለህ?
  «ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ» ብሎ ተሳድቧል። /ማቴ26፡65/
- ጲላጦስ፦ የአንተስ ሐሳብ ምንድር ነው?
  «በዚህ ሰው አንዳች በደል አላገኘሁበትም» /ሉ.23፡4፣14፣22/
- ይሁዳስ?፦ ጌታህን ስለብር ብለህ ሸጠኸዋል፤ ስለእርሱ ምን አልክ?
  «ንጹሕን ሰው ነው እርሱን አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ» /ማቴ.26፡4/
- አንተስ፦ የመቶ አለቃ?
  «ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ» /ማር.15፡39/
- መጥምቁ ዮሐንስስ?፦ ስለክርስቶስ ምን ታስባለህ?
  «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» /ዮሐ1፡29፣36/
- ሐዋርያው ዮሐንስስ፦ ምን ትላለህ?
  «የሚያበራ የንጋት ኮከብ»/ራእ.22፡16/
- ጳውሎስስ፦ አንተስ ስታሳድደው ነበርህ፤ ምን ትላለህ?
  «በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለክርስቶስ ኢየሱስ ስለጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ»/ፊል.3፡8/
- ጴጥሮስስ፦ ስለ ጌታህ ምን ትላለህ?
  «አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» /ማቴ16፡16፤ ዮሐ6፡69/
- አንተስ ቶማስ?፦ ትንሣኤውን ስትጠራጠር ነበርክ ስለእርሱ ምን ትላለህ?
  «ጌታዬና አምላኬ» /ዮሐ.20፡28/
- የሰማይ መላእክትስ፦ ስለ ኢየሱስ ምን ትላላችሁ?
  «መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ነው»/ሉ.2፡11/
- ሁሉን ነገሮች የምታውቅ በሰማይ የምትኖር አብስ ምን ትላለህ?
  «በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት።» /ማቴ3፡17፤ማር.9፡7/

**አንተስ አንባቢ ስለ ክርስቶስ ምን ትላለህ?**

## ክርስቶስ ከዚህ ዓለም በአካለ ሥጋ ሲለይ

- ከረጢቱን ........ ....ለይሁዳ /ዮሐ12፡6/
- ሥጋውን ....... ....ለአርማትያሱ ዮሴፍ /ሉ.23፡50-53/
- እናቱን ... ... .. ..ይወደው ለነበረው ደቀመዝሙር /ዮሐ.19፡26/
- ልብሱን ......... ....ለጭፍሮች /ዮሐ19፡23-24/
- ሰላሙን ......... ....ለደቀመዛሙርቱ/ዮሐ.20፡19-20/
- እራቱን ......... ....ለተከታዮቹ /ሉ22፡14-23/
- ምሳሌነቱን........ .....ለአገልጋዮቹ /ዮሐ13፡15/
- ወንጌሉን ........ .....ለዓለም /ማር.16፡15/

በመካከላቸው ሁልጊዜ መገኘቱን ..........በስሙ ለሚሰበሰቡት /ማቴ18፡20/

**ተወ፡፡**

## ሐኪሙን ወይስ የሐኪሙን እናት?

ከጌታ ይልቅ በጌታ እናት በቅድስት ማርያም የሚታመኑ አንዲት እናት ነበሩ ፤ በአንድ ወቅት በጠና ታመሙና በኢየሱስ ብቸኛ አዳኛነት ያምን የነበረውን ልጃቸውን «እባክህ ሐኪሙን ጥራልኝ» በማለት ወደሐኪም ላኩት፤ ልጃቸውም በዚያ አጋጣሚ ለእናቱ ስለኢየሱስ ሊመሰክርላቸው ስለፈለገ ሄዶ ሐኪሙን ሳይሆን የሐኪሙን እናት ጠርቶላቸው መጣ፤ የሐኪሙ እናት ሐኪም አለመሆናቸውን የተረዱት እናቱም «ሐኪሙን እንጂ እናቱን ጥራልኝ ብዬሃለሁን?» ባሉት ጊዜ «ምነው እናትና ልጁ አንድ ናቸው ትዪኝ አልነበረምን?» ሲል ጠየቻው የሚመልሱለትን መልስ በጉጉት በመጠባበቅ፤ እርሳቸውም መልሰው «ምን አገናኘው? እኔ የሐኪም እናት እና ሐኪም አንድ ናቸው ብያለሁ?» እርሱም ቀበል ብሎ «እየሽ እማ የሐኪሙ እናት ሐኪም መሆን እንደማይችሉ ሁሉ የአዳኙ የኢየሱስ ክርስቶስም እናት አዳኝ መሆን አትችልም መዳንም በኢየሱስ ክርስቶስ ካልሆነ በቀር በሌላ በማንም የለም » በማለት የሐ.ሥ.4፡12 ን ጠቅሶ መስከረላቸው፤ ከዚያም ከጠራቸው ከሐኪሙ እናት ጋር እንዲወያዩ ትቷቸው እርሱ ሐኪሙን ሊጠራላቸው በፍጥነት ሄደ፤ ምስክርነቱም በልባቸውም ተጻፈ፡፡

# አዲስ ቅኔ ለበጉ

## ከተዋጁት

## ኢየሱስ ለእኔ

*ኢየሱስ ለእኔ*
*... ...መድኅኔ*
*ያወጣኸኝ ከኩነኔ*

ለአእምሮዬ ነህ ሰላሜ
ፍጹም እረፍት ለድካሜ
እንጀራ ነህ ለሕይወቴ
እርካታዬ ለጥማቴ
መሸሸጊያ መመኪያዬ
ከሞት ፍርሃት ማምለጫዬ፡፡
ከመቅበዝበዝ ያረፍኩብህ
ሸክሜን ሁሉ የጣልኩብህ
የማትሰለች እረኛዬ
የማትደክም ጠባቂዬ
አንተን ብዬ አላፈርኩም
ተደግፌህ አልወደቅሁም፡፡

አባት፣እናት፣እህት፣ወንድም
ንጉሥ፣ጌታ፣ለዘላለም
ዘይት ይገባ ምጠብቅህ
ጠዋት ማታ ምናፍቅህ
የዘላለም ሽልማቴ
አክሊሌ ነህ መድኃኒቴ፡፡
ውበት የለኝ ውበቴ ነህ
ክብርም የለኝ ክብሬ አንተ ነህ
ደም ግባቴ መዓዛዬ
ጌጤ አንተ ነህ መዋቢያዬ
የጠላቴን ፍላጻውን
እኔን አጥፊ መዣሪያውን
መመከቻ ጋሻዬ ነህ
ጽኑ ግንቤ ኢየሱስ ነህ፡፡

አለቴ ነህ መሠረቴ
ራሴ ነህ ጉልላቴ
ጉልበቴ ነህ ለድካሜ
ፈውሴ አንተ ነህ ለህመሜ፡፡

በጨለማ በሞት ጥላ
ለነበርኩኝ በአውላላ
ፀሐየ ጽድቅ ሆነህልኝ
ጨለማዬን ገፈፍክልኝ
ዛሬማ አንተን ያየል ዓይኔ
ሆነህልኝ ብርሃኔ፡፡

መንገድ፣ሕይወት፣ፍጹም እውነት
ወደ እግዚአብሔር ምቀርብበት
መሰላል ነህ ለእኔነቴ
መድረሻዬ ወደ አባቴ
ወዳጄ ነህ አለኝታዬ
የቅርብ አጽናኛ መካሪዬ
ጓዳዬ ነህ የምሥጢሬ
የነፍሴ አባት መምህሬ፡፡

ጻድቅ ሆነህ ያጸደከኝ
ቅዱስ ሆነህ የቀደስከኝ
የማለድከው ስለ እኔ
ኢየሱስ ነህ ሊቀ ካህኔ
የሞት ቀንበር ተጭኖብኝ
የሲኦል ደጅ ሲያስጨንቀኝ
ሞቴን ሞተህ አሳረፍከኝ
ትንሣኤና ሕይወት ሆንከኝ፡፡

ቀና ብዬ ወደ ሰማይ
የእግዚአብሔርን መቅደሱን ሳይ
ታማኝ ካህን መሥዋዕቴን
ቆሞ አየሁት በረከቴን፡፡
9

ዓመፃዬ ሳይታሰብ
በንጉሡ በእግዚአብሔር ልብ
ዋስ ጠበቃ ሆነህልኝ
በአባትህ ፊት ታየህልኛ፣
አንተ በዚያ በመኖርህ
እኔም ባንተ አረፍኩብህ፡፡

በንጉሥ ቀኝ በዙፋኑ
ትምክህት ሆኖ ለወገኑ
ሥፍራ ይዞ ሚጠብቀኝ
ጠበቄ የሱስ አለኝ
አለኝ አባት የሚያኮራ
ስለ እኔ የሚራራ
ደግሞም አለኝ ኃያል ንጉሥ
ጥያቄዬን የሚመልስ
ከሰሎሞን የሚበልጠው
እንቆቅልሼን የፈታው
የሱስ ለእኔ ጥበቤ ነው፡፡

በመሆንህ አንተ የእኔ
ወግ አየሁኝ በዘመኔ
ስለበዛብኝ ውለታህ
ጌታዬ ሆይ ማን ልበልህ?
ስያሜ አጣሁ ለአንተነትህ
ል የለኝም የሚገልጥህ
ፍጹም ምሉዕ ሆነህልኝ
የእኔ ያልኩትን ጥያለሁኝ
አትጠገብ ጠዋት ማታ
ሁሉንም ነህ የኔ ጌታ
እንዲያው ልበል የሱስ ለእኔ
ሁሉንም ነህ መድኅኔ፡፡



## የምታገለግሉት ጌታ..

ከገጽ 12

እውቅና ለማግኘት ወይም ዝነኛ ለመሆን ሲሉ ያልሆኑትን ሆነን ነበር የሚሉ፣ ያልደረሰባቸውን ደረሰብን፣ ያልተቀበሉትን ተቀበልን በማለት የሚዋሹ፣ በሕዝብ ፊት ሲቆሙ ከሌላው አገልጋይ በላይ ለመሆን ሲሉ የውሸት ድርሰቶቻቸውን ፈጥረው ህዝብን ለማስፈንደቅና ለማሳቅ ሲሉ ለዓለም ወደሚመች ተረት ፈቀቅ ያሉ ሰዎች የሚያገለግሉት ማንን እንደሆነ አወቀው ይህን ዓይነት አድራጎታቸውን ቢተዉ መልካም ይሆንላቸዋል።

### 3. <u>የሃይማኖት ድርጅትን ፊድ ክርስቶስ ፈድ ማስቀደም</u>

የአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች በሸንጎ አቁመው በኢየሱስ ስም እንዳያስተምሩ ሐዋርያትን ባዘዟቸው ጊዜ ጴጥሮስና ዮሐንስ የመለሱትን ቁርጠኛ መልስ መመልከቱ ከክርስቶስ ፈድ ይልቅ የሃይማኖት ድርጅትን ፈድ ማስቀደም ተገቢ እንዳልሆነ ለመረዳት ጠሚ ነው። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ስለዚህ ጉዳይ የተጻፈው ቃል «ጠርተዋቸውም በኢየሱስ ስም ፈጽመው እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዙአቸው። ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን መልሰው እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደሆነ ቁረጡ/ለዩ/፤ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም አሉአቸው» ይላል /ሐ.ሥ4፡18/። በሌላ ጊዜም ሐዋርያትን «በሸንጎ አቁመዋቸው በዚህ ስም እንዳታስተምሩ አጥብቀን አላዘዝናችሁምን?» በማለት ሊቀ ካህናቱ ሲናገራቸው «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል» ብለው መልሰዋል /ሐ.ሥ.5፡29/። ስለሆነም በዚህ ዘመን ከክርስቶስ ይልቅ አንድ ቤተ እምነትን ደስ ለማሰኘት ሲሉ የሃይማኖት ድርጅት መልእክተኛ በመሆን የክርስቶስን ሀሳብ ወደጎን የጣሉና በሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ ሠርጎ የገባውን የሰው ሐሳብና ሥርዓት እያራመዱ አገልጋይ የተሰኙ ሰዎች ከዚህ ተምረው የክርስቶስ መልእክተኛ ወደ መሆን ሊመጡ ይገባቸዋል፤ ከአንዱ ሥፍራም ወደ ሌላው ሥፍራ መሄድ ያለብንም የክርስቶስ መልእክተኞች ሆነን ነው። ስለዚህም ጳውሎስ ሲጽፍ «የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃጡ እንደ ብዙዎች አይደለንምና፤ በቅንነት ግን ከእግዚ አብሔር <u>እንደተላክን</u> በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን» /2ቆሮ2፡17/ ሲል በሌላ ቦታ ደግሞ «ስለክርስቶስ <u>መልእክተኞች</u> ነን» ይላል /2ቆሮ5፡20/። አገልጋዩ የድርጅት መልእክተኛ ከሆነ ግን በወንጌል ስብከት ሰዎችን የሚጠራው ወደ ክርስቶስ ብቻ ሳይሆን ወደ ላከው ድርጅትም ነው፤ ያመኑትንም እንኳ ሳይቀር ወደራሱ ድርጅት አፍልሶ የድርጅቱን ተቀጽላ መፍጠር ዋና አላማው ነው። ከክርስቶስ ትምህርት ይልቅ ስለራሱ ድርጅት የሚሰብክ ይሆናል፤ እንዲህ ዓይነቱ መልእክተኛ ሰዎችን የክርስቶስ ቅርንጫፍ በማድረግ ፈንታ የራሱ ድርጅት ቅርንጫፍ በማድረግ ይረካል፤ በክርስቶስ ስም እንዲጠሩ በማድረግም ምትክ በራሱ ሃይማኖት ስም እንዲሰየሙም ያደርጋል። በዚህ ዓይነት የሃይማኖት ድርጅት መልእክተኛ ሆኖ የሚያገለግል ሰው የማገለግለው ማንን ነው? ብሎ ራሱን ሊጠይቅ ይገባዋል።

ከመጀመሪያው በክርስቶስ የተላከ የክርስቶስ መልእክተኛ የክርስቶስን እንጂ የሰውን ሐሳብ የአገልግሎቱ ማዕከል አያደርግም። በሰው የተሰየሙና በሰው የተላኩ አገልግሎታቸውንም ከሰው የተቀበሉ አገልጋዮች ግን የላካቸውን ሰውና ድርጅት እንጂ የክርስቶስን ሐሳብ አያስቀድሙም፤ አይከተሉምም። ጳውሎስ ግን ስለተልእኮው ሲናገር «ከሰዎች ወይም በሰው ያልሆነ» ይላል /ገላ.1፡1/። አገልግሎቱን ከሰዎች ወይም በሰው ያላገኘና «በእግዚአብሔር አብ» አገልጋይ የሆነ ማንም ቢኖር የሚያስቀድመው የላኪውን ፈድ ነው፤ የሰውንም ሆነ የራሱን ወይም የሃይማኖት ድርጅት ባለሥልጣናትን ፈድ አያስቀድምም። ጌታ እግዚ አብሔር የፈዱን አገልጋዮች ይስጠን፤ አሜን። //

---

**በነጻ የሚታደል**

«እውነት» በየሁለት ወሩ እየተታተመ ለአንባቢያን በነጻ የሚታደል ጋዜጣ ነው።

**ለማገዝ ይፈልጋሉን?**

ጋዜጣውንም ሆነ ሌሎችን መጻሕፍት ለብዙዎች ማዳረስ እንድንችል እርስዎም የአቅምዎትን ገንዘብ በፖስታ ቤት <u>በሐዋላ</u> ለአሳታሚው ይላኩ። እርስዎ የሚልኩት ጥቂቱ ገንዘብ ሌሎችን የእግዚአብሔር ቃል እንዲያነቡ የሚያግዝ መሆኑን አይዘንጉ።

**መጻሕፍት?**

«የእውነት» ጋዜጣ አሳታሚ ቀደም ሲል አንድምታ ዝግጅት በተሰኘ ክፍሉ መንፈሳዊ መጻሕፍትን አሳትሞ ሲያሠራጭ የቆየ ሲሆን አሁንም ላልደረሳቸው አንባቢያን አዲስ የሚታተሙትን ጨምሮ በነጻ የሚልክ መሆኑን በደስታ ይገልጻል።

መጻሕፍቱንም ሆነ ጋዜጣውን ለማግኘት በአሳታሚው አድራሻ በመጻፍ ይጠይቁ
ወይም
በሚቀርብዎት አድራሻ በሚቀጥሉት ቍጥሮች ይደውሉ፤

| | |
|---|---|
| አሰላ | 02-311312 |
| ጎባ | 06-610779 |
| ጂማ | 07-112357 |
| ደብረብርሃን | 01-813147 |
| በደሌ | 06-450365 |

COPY RIGHT© BGNLJ

`EUNET´ IS PUBLISHED BY : BGNLJ- NON PROFIT ORGANIZATION DEVOUTED TO THE PROPAGATION OF BIBLE TRUTH

P.O.Box 14787
ADDIS ABABA
ETHIOPA

ቢጂኤንኤልጄ (BGNLJ)
ፖ. ሣ. ቍጥር 14787
<u>አዲስ አበባ</u>

ለ ________________________
________________________
________________________
________________________
________________________
________________________